«ከመረጥኋቸው ጋር ቃልኪዳን አደረግሁ»
መዝ. ፹፰፥፫

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



# የወንጌል አገልግሎት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተጠቆመ

*ካሳሁን ለምለሙ*

የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የበላይ ኃላፊ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ መግለጻቸውን ኢ.ኦ.ተ.ቤ ቲቪ ዘገበ፡፡

ብፁዕነታቸው ይህንን የተናገሩት ስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የካቲት ፲ ቀን  ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባተዘጋጀው የአሠልጣኞች ሥልጠና መርሐ ግብር ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት አባታዊ መልእክት ነው፡፡

በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ በኩል የተዘጋጀው የአሠልጣኞች ሥልጠና  በሰሜን ኢትዮጵያና በኦሮሚያ ክልሎች ለሚደረገው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ስምሪት አጋዥ እንዲሆን ታስቦ የተሰጠ መሆኑን ብፁዕነታቸው አስረድተው አንዳንዶች የስብከተ ወንጌልን አገልግሎት የኑሮ መደጎሚያ ከማድረግ ወጥተው ምእመናን በቤቱ ጸንተው እንዲኖሩና የዘለዓም ሕይወትን በሚያገኙበት መንገድ አገልግሎት መስጠት አለባቸውም ብለዋል፡፡ ብፁዕነታቸው አያይዘው በአንዳንድ ገዳማትና አድባራት እስከ ፲፰ የሚደርሱ ሰባክያነ ወንጌል መኖራቸውን በመጥቀስ በገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን የሚስተዋለውን የሰባክያነ ወንጌል እጥረት ማሳየታቸውን ዘገባው አስረድቷል፡፡

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ አገልግሎት የቤተ ክርስቲያን ዋና ተግባርና መገለጫ በመሆኑ በሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ መዋቅር ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል ሲሉ ብፁዕነታቸው መናገራቸውን ዘገባው አመልክቷል፡፡

በሥልጠና መርሐ ግብሩ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ፤ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ሊቀ አእላፍ በላይ መኮንን፣ በመምሪያው ሥር ያሉና ከሌሎች ስድስት መመሪያዎች ጥሪ የተደረገላቸው ሰባክያነ ወንጌል ተገኝተዋል፡፡



መጋቢ ሐዲስ አእምሮ ደምሴ



ፈለገ ጥበብ በየነ ድንቄ

# የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት ለማስጠበቅ የአባቶችና የምእመናን ድርሻ ከምንጊዜው የተሻለ ሊሆን እንደሚገባ ተገለጠ

*ካሳሁን ለምለሙ*

የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት ለማስጠበቅ የአባቶችና የምእመናን ድርሻ ከምንጊዜው የተሻለ ሊሆን እንደሚገባ በሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ ኪዳን መምህርና በማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል የኤዲቶርያል አገልግሎት ማስተባበሪያ አርታኢ የሆኑት መጋቤ ሐዲስ አዕምሮ ደምሴ ገለጡ።

የቤተ ክርስቲያንን መብትና ክብር ለማስጠበቅና ታሪካዊና ጥንታዊ ይዞታዎቿን ለማስከበር እንዲሁም መንግሥት የሚያደርስባትን መዋቅራዊ ጫና ለመቋቋም የአባቶችና የምእመናን ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ያነሱት መጋቤ ሐዲስ አእምሮ ሁለቱ ባለድርሻ አካላትም የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር ተጠቅመው ሕጋዊ ትግል በማካሄድ የቤተ ክርስቲያንን የቦታ ይዞታዎች ሊያስከብሩ እንደሚገባ አንሥተዋል።

መንግሥት ቤተ ክርስቲያን የሀገር ባለውለታ መሆኗን ዘንግቶ በየጊዜው በደል ከመፈጸም ባሻገር በሕገ ወጥ መንገድ ቤተ ክርስቲያንን እየበደሉ ባሉ ሕገ ወጥ አካላትም ላይ የእርምት ርምጃ ባለመውሰዱ የቤተ ክርስቲያን ፈተና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ መምጣቱን መጋቤ ሐዲስ አእምሮ ጠቁመዋል።

በተለይ በዐደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ላይ በግልጽ የሚፈጸሙ በደሎችና የምእመናን በየጊዜው መገደል ቤተ ክርስቲያን በየአቅጣጫው የግፈኞች የጥቃት ሰለባ መሆኗን የሚያመላክቱ ተግባራት ናቸው ያሉት መጋቤ ሐዲስ አእምሮ በግፈኞች ግፍና በደል እየደረሰባቸው ያሉትን ገዳማትና አድባራትም መታደግ እንደሚገባም አሳስበዋል። መንግሥትም የቤተ ክርስቲያንን መብት አክብሮ ሊያስከብርላት እንደሚገባም አክለዋል።

‹‹የቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት ሊጠበቅ ያልቻለው አባቶችና ምእመናን ክብራቸውን ማስጠበቅ ባለመቻላቸው ነው” ሲሉ የተናገሩት ደግሞ በማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል የኤዲቶርያል አገልግሎት ማስተባበሪያ አርታኢ የሆኑት ፈለገ ጥበብ በየነ ድንቄ ሲሆኑ ከዚህ ቀደም የነበሩ አባቶቻችን ለቤተ ክርስቲያን ክብርና ነጻነት ሲሉ ራሳቸውን ለመሥዋእት ማቅረባቸውንም ተናግረዋል።

አያይዘውም ቤተ ክርስቲያን ውጫዊ ፈተናዎችን ለመሻገር ውስጣዊ አሠራሯን ማዘመንና መፈተሽ እንደሚገባት ያነሱት ፈለገ ጥበብ በየነ ድንቄ ወስጣዊ አሠራሯ ከተሻሻለ ውጫዊ ፈተናዎችን በጋራ ለመመከት የሚያስችል አቅም እንደሚፈጥርም አስገንዝበዋል። የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠንቅቀው የተማሩና ቀኖናዋንና ትውፊቷን በደንብ ለተረዱ አካላት ቦታና ድርሻ በመስጠት የቤተ ክርስቲያንን የመከራ ዘመን ማሳጠር እንሚቻልም አክለዋል።

በመጨረሻም አባቶች የወጣቶችን ፍላጎት ማወቅና በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ሥር ገብተው ሰላማዊ ትግል እንዲያደርጉ እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው የጠቆሙት ፈለገ ጥበብ በየነ “ቤተ ክርስቲያንም ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮቿን ለመፍታት ከተናጠል ጉዞ ይልቅ የአንድነት ጉዞ ብታደርግ ጥሩ ነው” ሲሉ ተናግረዋል።

# ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የተባበረ ኦርቶዶክሳዊ ኃይል ያስፈልጋታል

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ ስታልፍ ቆይታለች። በረጅሙ የአገልግሎት ዘመን ውስጥ መልካቸውን እየቀያየሩ በሚከሠቱ እና እየከበዱ በመጡ ተግዳሮቶች ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጠረ ያለው አሉታዊ ጫና ዛሬ ላይ ትልቁን የወንጌል አገልግሎት በምትፈልገው መጠን እንዳታካሂድ አድርጓታል። አስተዳደራዊ መዋቅሯ እንዲላላ፣ ተከታይ ምእመናኗ በነፃነት የአምልኮ ሥርዓት እንዳይፈጽሙ ሳንካ የሚሆኑ ምክንያቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።

የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያሳድዱ፣ በተለያየ መልክ ሲፈትኑ የነበሩ ፀረ መስቀል ኃይሎች በጥፋታቸው ቀጥለው አካሉ የሆነችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በማሳደድ፣ ተከታይ ምእመናንዋን በመግደል፣ ንዋያተ ቅድሳቷን በመዝረፍ ዛሬ ድረስ ዘልቀዋል። ይባስ ብለው ለጥፋት ተልእኮአቸው ሽፋን የዳቦ ስም በማውጣት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለውን በደል ሚዛናዊ፣ ምክንያታዊ፣ ፍጹም ትክክልና የራስዋ የቤተ ክርስቲያን ጥፋት በማድረግ ላይም ይገኛሉ።

የጥፋት ተልእኮአቸው እንደየዘመኑ፤ እንደየ ርእዮተ ዓለሙ፣ እንደየአካባቢው ዘርፈ ብዙ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ ጠብቃ የቆየችውን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አልባ ለማድረግ የሚደረገው ሽኩቻ ቀላል አይደለም። ሀገርን ያህል የሚመሩ ነገሥታትን ቅብዐ መንግሥት ስትሰጥ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን «የጨቋኞች መሣሪያ ናት» የሚል ታርጋ በመለጠፍ ሰድበው ሰዳቢ ትውልድ እንዲፈጠር አድርገዋል። ፈጥረው በነዙት የሐሰት ትርክት ብዙኃኑ እይታው እንዲንሸዋረር ሲያደርጉት ኖረዋል። በዚህም ምእመኑ ቤተ ክርስቲያንን በጥርጣሬ ዓይን እንዲያይ ፖለቲካዊ ጫና ፈጥረውበታል።

ዓለም አቀፋዊቷን ቤተ ክርስቲያን የአንድ አሊያም የተወሰነ ብሔር ሃይማኖት እንደሆነች አድርጎ በማቅረብ፣ በማሳየት በተቃራኒው የአንተ ሃይማኖት አይደለም በተባሉት ዘንድ በአይነ ቁራኛ እንድትታይ የተካሄደው ዘመቻ ቀላል አይደለም። በዚህም የተነሳ ታላቋ ቤተ ክርስቲያን ተሰሚነቷ፣ መከበሯ፣ መፈራቷ እንዲቀንስ ሰፊ ሥራ ሲሠራባት ኖሯል።

ሥር እየሰደደ የመጣው እና ዛሬ ላይ በቅንጅት እየሠራ ያለው ፀረ ኦርቶዶክስ ዘመቻ ተከታይ ምእመናንዋን እያሳደደ፣ ቤተ ክርስቲያንን እያቃጠለና እየዘረፈ፣ ነባር ይዞታዎቿን በተለያየ መንገድ እየቀማ ታሪክ አልባ፣ ምእመናን አልባ፣ ይዞታ አልባ የማድረግ የረጅም ጊዜ እቅዱን እየተገበረ ይገኛል። አንዳንዱ ጋር ሃማኖታዊ፣ ሌላው ጋር የጎጥ እንዲሁም አንዳንዱ መዋቅራዊ ይዘት ባለው በእንዲህ ዓይነቱ ፀረ ኦርቶዶክስ ዘመቻ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ ፈተና መለየትና ዘላቂ መፍትሔ መፈለግ ከቤተ ክርስቲያን እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ብዙ ሥራ ይጠበቃል።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሁለንተናዊ አገልግሎት ለማዳከም ብሎም ለማጥፋት ከውስጥ የጀመረውን ቤተ ክርስቲያንን እና አባቶችን የመከፋፈል፣ አስተምህሮዋን የመበረዝ ጠንካራውን መዋቅር የመበጣጠስ እንዲሁም በሂደት የማጥፋት እንቅስቃሴ በትዕግሥት እና በአስተዋይነት ማስተካከል ይገባል። በውስጥ ያለውን ችግር በመወያየት መፍታት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተቃጣ ያለውን ውጫዊ ጫና በብዙ መልኩ ይቀንሳልና ሊታሰብበት ይገባል። ቤተ ክርስቲያንን ወደ ቀደመ

ክብሯና መፈራቷ እንድትመለስ ከላይኛው የሲኖዶስ አካል ጀምሮ እስከ ታችኛው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድረስ ያለው የቤተ ክርስቲያን አካል እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ አሳቢ በመሆን መሥራትን ይጠይቃል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በተለያየ አቅጣጫ የተከፈተባትን የጥፋት ዘመቻ ለዘመናት ተሸክማ በትዕግሥት ማሳለፏ እንደፈሪ ወይም እንደለዘብተኛ ሊያስቆጥራት አይገባም፡ ፡ እንደ ቀዳሚነቷና አንጋፋነቷ ልትከበር ልትፈራ እንደሚገባ ልጆችዋ በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ የመዋቅሯን ቅደም ተከተል ማስጠበቅ፣ የላይና የታች ግኑኝነትን ማጠናከር፣ የበላይ አካልን መስማትና ማክበር ጠላቶቿ እንደክፍተት ያዩትን አንድ ቀዳዳ ይደፍናልና በተግባር ሊገለጥ ይገባል።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መገፋት፣ መዋረድ፣ መሰደድ ለሁሉም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች እኩል ሊቆጨን ይገባል። እነ እገሌ ይታገላሉ በሚል የተቆርቋሪ፣ የአድራጊ ተመልካች መሆን የራስን ድርሻ አለመወጣት በቤተ ክርስቲያን እና በእግዚአብሔር ፊት ከመጠየቅ አያድንም። ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ላይ እየተካሄደ ያለውን የጥፋት ዘመቻ ሁሉም ምእመን በንቃት የሚከታተለው፣ ለምን ብሎ የሚጠይቀው፣ በሚፈለግበት እና በሚጠራበት ቦታ ሁሉ አለሁ ብሎ የሚገኝ መሆን ይጠበቅበታል።

የቤተ ክርስቲያንን ሰቆቃ ለማስቆም፤ ወደ ቀደመ ክብሯ እንድትመለስ ለማድረግ በአጥቢያ፣ በማኅበራት፣ በቡድኖች፣ በተለያዩ ግለሰቦች የሚደረገው እንቅስቃሴ ይበል የሚያሰኝ ቢሆንም ተበታትኖ የሚደረግ ትግል በተናጠል ለመጠቃት ከመዳረግ ውጪ ቤተ ክርስቲያንን ብዙ አይጠቅምም። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የተባበረ ኦርቶዶክሳዊ ኃይል ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ አባቶችን የሚሰማ፣ ምክራቸውን የሚያዳምጥ እነርሱ በሚሰጡት አቅጫ የሚጓዝ አባቱን አክባሪ ትውልድ ያስፈልጋታል። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ በፈረሰው በኩል የሚቆም ለእምነቱ ቁርጠኛ ኦርቶዶክሳዊ ምእመን ያስፈልጋታል። «ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር» እንዲሉ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚቃጣውን ጥቃት ለመከላከል አንድነት፣ መተባበር መስማማት ጊዜው የሚጠይቀው ዐቢይ ጉዳይ ነው።

ቤተ ክርስቲያን ጠንክራ እንድትቆም ማስቻል ሀገር ጠንክራ እንድትቆም አንድ እንድትሆን ማስቻል መሆኑን ሁሉም መዘንጋት የለበትም። ሀገርን ከማፍረስ አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያንን የማጥፋት እና የማፍረስን እኩይ ተግባር ጠንክሮ መቃወም እየባሰ የሚመጣውን የቤተ ክርስቲያን ሰቆቃ መቀነስ ብሎም ማስቆም ነውና በኅብረት የሚሰማ ጠንካራ ድምፅ ያስፈልጋል።

ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣትን የወንጌል አገልግሎት ተልእኮ በነፃነት ለመወጣት፣ ምእመናንም ካለተፅዕኖ እምነታቸውን እንዲያራምዱ፣ ተሸማቀው ሳይሆን ቀና ብለው እንዲሄዱ ወጥነት ያለው ኅብረታዊ ሥራ ያስፈልጋል። በሰበብ አስባቡ እየተነጠቀች ያለውን ይዞታዎች ለማስመለስ፤ እየተገደሉ ላሉ ምእመናንዋ ፍትሕ ለመጠየቅ ከግለሰብ ጀምሮ የምእመናን፣ የወጣቶች፣ የማኅበራት፣ የአባቶች አንድነት፤ የአብያተ ክርስቲያናትና የገዳማት ኅብረት ፤የሀገር ውስጥ እና የውጭው ዓለም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች መስተጋብር የሚያስፈልግበት ወቅት ነውና ለዚህ ኅብረት ልንተጋ ይገባል።

# የምእመናን ዜግነታዊ መብቶች ይከበሩ፤ የቤተ ክርስቲያንም ሉዓላዊነት ሳይሸራረፍ ይረጋገጥ!!

ክፍል ሁለት

ሻምበል ጥላሁን

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

በመቀጠልም "ከዚህም የተነሣ በገጠር የተጀመረው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዐደባባይ በዓላት የምትጠቀምባቸውን የአምልኮ ቦታዎች መቀማትና ለሌላ አገልግሎት መስጠት እያደገ መጥቶ በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓል የምታከብርበትን የመስቀል በዓል ማክበሪያ ቦታ ከዓላማው ጋር በማይሄዱ ለሌላ አገልግሎት የማዋልና ለሌሎች አሳልፎ የመስጠት ሙከራዎችን ማየታችን ጥቃቱ ከፍተኛ ደረጃ ለመድረሱ ማሳያ ነው" ሲልም አብራርቷል።

ማኅበሩ ባወጣው የአቋም መግለጫ አያይዞም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በውጭ እና በውስጥ በሚደርስባት ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ምእመናን ፣ እንዲሁም በተለያዩ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ያሉ አካላት ቤተ ክርስቲያን ስደት ላይ መሆንዋን ተረድተው፦ አባቶች የቤተ ክርስቲያንን ስደት ለመቀበል መዘጋጀት እንዳለባቸው፤ የቤተ ክርቲያን አካላት ሆነው ነገር በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ባለው ጥቃት ውስጥ ከመሳተፍ እንዲቆጠቡ፣ በቤተ ክርስቲያን የኃላፊነት ቦታ ያሉና ለጊዜያዊ ጥቅምና ፍላጎት መጠቀሚያ የሆኑ አካላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ፤ እንዲሁም መንግሥት ውሳኔዎችን ሲወስን አሁን እየታየ ባለው መልኩ በጨኸትና የቤተ ክርስቲያንን መብት በመግፋት ፍትሕ እያዛባ የሚሄድና በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለው ስደት እንዲቆም የማድረግ ድርሻውን የማይወጣ ከሆነ ለሚደርሰው ሰላም ማጣትና ችግር ኃላፊነቱን የሚወስድ መሆኑን ማሳሰቢያ መስጠቱና መጠየቁ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ይሁን እንጂ መንግሥት ኀላፊነቱን እንዲወጣ፡ የምእመናንን ዜግነታዊ መብቶች እንዲያከብርና፤ የቤተ ክርስቲያንም ሉዓላዊነት ሳይሸራረፍ እንዲያረጋግጥ እነዚህ ሁሉ መግለጫዎችና ማሳሰቢያዎች ቢቀርቡም በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰው ስልታዊና መዋቅራዊ ጥቃት ተጠናክሮ ቀጠለ እንጂ አልቀመም። በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰው እንዲህ ዓይነቱ ስልታዊና መዋቅራዊ ጥቃት ተጠናክሮ መቀጠሉን የሚያሳዩ፤ ዛሬም ድረስ ቀጥለው የቤተ ክርስቲያን እና የምእመናን ተግዳሮት ከሆኑት ውስጥ የሚከተሉት ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው።

**የመስቀል አደባባይ ጉዳይ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዐደባባይ የምታከብራቸው ሁለት ዐበይት በዓላት የመስቀል እና የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀት በዓላት ትልቅ ሥፍራ የሚሰጣቸው ናቸው።

ቤተ ክርስቲያን የባለቤትነት መብትዋ ተገፎ የመስቀል ዐደባባይ በሌሎች የሃይማኖት ድርጅቶች እንዲነጠቅ መዋቅራዊ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸው ይህም ወደ ተግባር ተለውጦ ጥር ፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በዐደባባዩ የሌሎች እምነት ተከታዮች ጉባኤ ማድረጋቸው ከመንበረ ፓትርያርክ ጀምሮ ብዙኃኑን ሕዝበ ክርስቲያን ያስቆጣ የቅርብ ጊዜ ድርጊት ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ በወቅቱ በመስቀል ዐደባባይ ላይ የተፈጸመውን እኩይ ድርጊት በመቃወም እና ውዝግቡን ለመፍታት አስቸኳይ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ጠርቶ ማወያየቱ የሚታወስ ሲሆን፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትም በጉባኤው ተገኝተው ስለ ጉዳዩ እንዲያስረዱ ጥሪ ተደርጎላቸው የነበረ ሲሆን በወቅቱ ቅዱስ ፓትርያርኩ ባጋጠማቸው የጤና እክል ምክንያት ጉዳዩ በቀጠሮ እንዲያዝና ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን በትኩረት እንዲከታተሉት መደረጉ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ በባለቤትነት የሚከታተሉ አካላት በወቅቱ ካወጧቸው የአቋም መግለጫዎች መገንዘብ ይቻላል።

ማኅበሩ ችግሩን ከመነሻው ጀምሮ በቅርበት እየተከታተለ መሆኑን ጠቅሶ ‹‹ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርያንን ክብር በሚመጥን ደረጃና ሀገራዊ ኃላፊነትን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ችግሩን ለመፍታት እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው›› ሲል ጠቅሷል። አያይዞም ‹‹በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ያሉ አንዳንድ ግለሰቦች የቤተ ክርስቲያንን ልዕልና፣ ክብርና ጥቅም በሚጻረር መልኩ እያደረጉ ካለው ያልተገባ እንቅስቃሴ እንዲቆጠቡ በዚሁ አጋጣሚ በጥብቅ እናሳስባለን›› ሲልም በመግለጫው መልእክቱን አስተላልፏል።

በኦርቶዶክሳዊነታቸው ብቻ ለተደጋጋሚ ጥቃት እየተዳረጉ፣ የግፍ ግፍ እየተፈጸመባቸው ለሚገኙ ምእመናን የሕይወት ዋስትና መረጋገጥ እና ለቤተ ክርስቲያን ህልውና መቀጠል፣ ወጣቶችንና ምእመናንን በአንድነት አስተባብሮ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ጴጥሮሳውያን የቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት አስጠባቂ ኅብረት በበኩሉ ጥር ፳ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባወጣው መግለጫ "የአዲስ አበባ መስተዳድር ፍትሕ

የጠየቁ ክርስቲያኖችን ማዋከብና ማስፈራራት ያቁም” ሲል አሳስቧል፡፡ ኅብረቱ በመግለጫው ‹‹በሰማዕታት ደም ፪ ሺህ ዓመታትን ተሻግራ፣ ጸንታ የቆመች የቤተ ክርስቲያን ልጆች እሥር እና ማዋከብ ከቆሙለት እውነት እና ከመሥዋዕትነት ፍኖት አያወጣቸውም›› ያለ ሲሆን አያይዞም “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መብቷን እየሠዋች መኖር በቃ እያለች ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ዋና ከተማውን ጨምሮ በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በመንግሥት አካላት እየደረሰባት ያለውን ታሪካዊ ይዞታዎቿን የመንጠቅ፣ አድሏዊነት የሰፈነበትን የመንግሥት ባለሥልጣናት አሠራር ከሥሩ ደርቆ ፍትሕ እንዲሰፍንላት በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃ አምርራ በመታገል ላይ ትገኛለች” ሲልም ገልጿል፡፡

ጴጥሮሳውያን አክሎም “ኦርቶዶክሳውያን ሁልጊዜ እያለቀሱ እንዲኖሩ፣ ቤተ ክርስቲያኗን ያለማቋረጥ ማሳደድ የሚሹት እነዚህ አካላት ከሕዝብ የተቀበሉትን ሥልጣን ለሚያምኑት እምነት መጠቀሚያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያንን ማዳከሚያ ማድረጉን ተያይዘውታል” ያለ ሲሆን ሕዝብን እንዲያገለግል የተቋቋመውን የፖሊስ እና የፀጥታ ኃይል ለአድሏዊ አመራራቸው ከለላ እንዲሆን በማዘዝ ከጥር ፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ  የወጣቶችና ጎልማሶች ማኅበራት ኅብረት አመራሮችን እና ‘የቤተ ክርስቲያን የመከራ ዘመን ይብቃ’ የሚሉ ኦርቶዶክሳውያንን ሁሉ በማሳደድና በማዋከብ ላይ እንደሚገኝም በመግለጫው ጠቁሟል፡፡

በ፳፻፲፬  ዓ.ም  በበዓለ ጥምቀት ላይ የተከሠተ ችግር

በቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለው አድሎአዊ አሠራር እና ኢፍትሐዊነት በመስቀል ዐደባባይ ላይ ብቻ ያበቃ አይደለም፡፡ የሺ ደበሌ አካባቢ የምትገኘው የወይ ብላ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታቦት ጥር ፲፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ወደ መንበሩ ሲመለስ ፖሊስና በአካባቢው ያሉ ወጣቶች በፈጠሩት ግርግር ሰላምን የሚያደፈርስ ችግር በመከሠቱ ታቦቱ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዳያልፍ ተከልክሏል፡፡ ከዚህም የተነሣ ታቦቱ ወደ ኋላ ተመልሶ በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ ተደርጓል፡፡

በወቅቱ ፖሊስ በምእመናንን ላይ አስለቃሽ ጭስ የተኮሰ ሲሆን ከአስለቃሽ ጭስ በተጨማሪ ወደ ምእመናን ላይ በተተኮሰ ጥይት በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ በነበሩ ሦስት ወጣቶች ላይ የተፈጸመው ግድያ ቤተ ክርስቲያንን እና ምእመናንዋን በእጅጉ ያሳዘነ በታሪክ ውስጥም ትልቅ ጠባሳን ጥሎ ያለፈ እኩይ ድርጊት ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

ጥር ፲፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ወደ መንበሩ ሳይመለስ በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ የተደረገው ታቦቱም ጥር ፲፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፡ የአድባራት አስተዳዳሪዎች እና በርካታ ምእመናን በተገኙበት ወደ መንበረ ክብሩ የተመለሰ ሲሆን፤ በግፈኞቹ የተገደሉት ሦስቱ ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን አባቶችና በርካታ ምእመናን በተገኙበት ሥርተ ቀብራቸው ተፈጽሟል፡፡ ሀገርን ከነድንበሩ፣ ነፃነትን ከነክብሩ ባስረከበችና ብራና ዳምጣ፣ ብዕር ቀርፃና ቀለም በጥብጣም የማይምነትን ጥላ በገፈፈችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእምናኖቿ ላይ ይህ ድርጊት በመፈጸሙ በርካቶቹን ያሳዘነና ያስቆጣ ሲሆን፡ ከሃይማኖት ተቋማት እስከ ፖለቲከኞች ጉዳዩን በማውገዝ አቋማቸውን እንዲገልጹም አስገድዷል፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጥር ፲፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባወጣው መግለጫ  ከጥምቀት በዓል አከባበር ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ  ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን በቡራዩ ከተማ አስተዳደር ሥር በምትገኘው የወይብላ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ታቦት ወደማደሪያው ለማስገባት በነበረው ሥነ-ሥርዓት ላይ በተፈጠረ አለመግባባትና ግጭት ሕይወታቸውን ስላጡት ወገኖቻችን የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን የገለጸ ሲሆን ለሟች ቤተሰቦች መጽናናትን ተመኝቷል፡፡ ጉባኤው አያይዞም ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለምእመናንና ለመላው ኢትዮጵያውያን አክብሮትንና ትሕትናን፣ ፍቅርና መከባበርን፣ ሰብአዊነትንና ሰላምን ስታስተምርና በማስተማር ላይ የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ ይታወቃል›› ያለ ሲሆን ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን የሰላም መሠረት በመሆን ዘመናትን እንደተሻገረች የጥምቀት በዓልም በቤተ ክርስቲያን በዐደባባይ ከሚከበሩት ታላላቅ በዓላት አንዱ መሆኑንና በተጨማሪም የበዓሉ ሥነ ሥርዓትም በዩኔስኮ ከተመዘገቡት ከማይዳሰሱ ቅርሶች አንዱ ሆኖ የተመዘገበ ዓለም  አቀፋዊ ክብረ በዓል  መሆኑንም ገልጿል፡፡

ቤተ ክርስቲያን የሀገር ክብርና ርስት መሆኗ ቢታወቅም ከውጭና ከውስጥ የተፈጠሩ ጠላቶች በየጊዜው ቤተ ክርስቲያንን እየተነኮሱ መብቷን ሲጥሱ ክብሯን ሲጋፉ ቆይተዋል፡፡

ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን እንደ አውሬ እያደኑ የመግደልና የሀገር ባለውለታ የሆነችው ይህችን ቤተ ክርስቲያን መሥዋዕትነት ሆና በመሠረተቻት ሀገር ርስት አልባ የማድረግ መከራው ከተጀመረ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው፡፡ ከዛሬ ሦስት ዓመት ጀምሮ በሀገሪቱ መጣ በተባለው ‹‹የፖለቲካ ለውጥ›› ሳቢያ አክራሪ ሃይማኖተኞችና የስሁት ትርክት አቀንቃኝ ፖለቲከኞች በጥምረት የሚመሯቸው የጥፋት ኃይሎች የቤተ ክርስቲያንን መብት ሲነጥቁና ርስቷንም እንደ ቅርጫ ሲከፋፈሉ እንደ ቆዩ ማሳያው ቤተ ክርስቲያን መብቷ እንዲከበር በተደጋገሚ ያወጣቻችው መግለጫዎች ናቸው፡፡

የሰሞኑም ጉዳይ አስመልክቶ የዩኬ እና አየርላንድ ማኅበረ ካህናትም በበኩላቸው "ለባለ ውለታዋ ቤተ ክርስቲያንና

ለተከታዮቿ የማይመጥን አሳፋሪ ድርጊትን እናወግዛለን" በሚል ጥር ፲፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም የአቋም መግለጫ አውጥተዋል፡ ፡ በመግለጫቸውም ‹‹የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ መሠረትነት ላይ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በፈተና ውስጥ እያለፈች አሁን ካለንበት ዘመን ደርሳለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዘመን መልኩን እና ሁኔታውን እየለዋወጠ የሚታየው ጦርነት የምእመናን በክርስትናቸው ምክንያት መገደል፣ የቤተ ክርስቲያን መቃጠል፣ የምእመናን መሰደድ እና ሀብት ንብረታቸው መዘረፍ  እጅግ ልብን የሚሰብር እና ከመቼውም በላይ የቤተ ክርስቲያንን ልዕልዕና የሚጋፋ እየሆነ መጥቷል›› ብለዋል፡፡

በተለይ የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ በሀገሪቱ በርካታ ስፍራዎች  የአምልኮ ቦታዎች መነጠቅ፣ ምእመኑ የዐደባባይ አምልኮ ሥርዓቱን  በአግባቡ እንዳያከብር በጥቂት በባለ ሥልጣናት ትእዛዝና ሕግ አስከባሪዎች የሚደርሰው ውክቢያ ይሻሻላል ተብሎ  ሲጠበቅ እየባሰና ግድያዎች እየተፈጸሙ ነው የሚለው የማኅበረ ካህናቱ መግለጫ፤ “የሀገር እና የቤተ ክርስቲያን መለያ የሆነውን አርማ ‹አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ መያዝ የለበትም› በሚል ሰበብ በወይብላ ማርያም ችግር ሲፈጠር ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡  ባለፈው ዓመትም በነበረ ተመሳሳይ ችግር የሚመለከተው አካል ችግሩን መፍታት ባለመቻሉ የሰዎች ሕይወት እንዲያልፍ ምክንያት ሆኗል” ሲል ይገልጻል፡፡ መግለጫው አያይዞም “እንዲህ አይነቱ ተግባርም በእቅድና በዝግጅት የሚከናወን በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያንን መገፋት በተመለከተ የሚወስናቸውን ውሳኔዎችና የሚያወጣቸውን መመሪያዎች እንደ ልጅነታችን ለመተግበር መዘጋጀታችንንም እንገልጻለን” የሚለው የማኅበረ ካህናቱ መግለጫ “የሰማዕታቱ በረከት ለሁላችን ይድረሰን፤ ለቤተሰቦቻቸውም መጽናናትን እንመኛለን” ብሏል፡፡

ሀገር አቀፍ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት በበኩሉ ድርጊቱን በማውገዝ ጥር ፲፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም  ባወጣው መግለጫ “ጥር ፲፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በየሺ ደበሌ አካባቢ በምትገኘው የወይ ብላ ቅድስት ማርያም ታቦትን አክብረው በሚመለሱ ካህናት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች እና አዛውንት ፣ ጎልማሳና ወጣት ምእመናን ላይ ለጸጥታ ማስከበር ሥራ በተሰማራ የጸጥታ አካል ኃይል በተሞላበት ጥቃት ምክንያት የደረሰው ችግር በተደጋጋሚ አንድ አካባቢ ሆን ተብሎ ሃይማኖታዊ ሥርዓታቸውን የሚፈጽሙ ክርስቲያኖችን ከማወክ አልፎ ለሞት መዳረጉ በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚድረስውን በደል የሚያሳይ  ኢ ሰብአዊና ኢ ፍትሃዊ ነው›› ሲል ድርጊቱን ተቃውሟል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ - (ኢሰመጉ) በበኩሉ ‹‹ መንግሥት የዜጎችን የሃይማኖት ነፃነት እና በሕይወት የመኖር መብቶችን ያክብር! ያስከብር!›› በሚል ባወጣው የአቋም መግለጫ “ የጥምቀት በዓልን ተከትሎ ጥር ፲፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ወጥቶ የነበረውን የወይብላ ማርያም ታቦት ጥር ፲፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም የቤተ ክርስቲያን አባቶች እና ሕዝበ ክርስቲያኑ አጅቦ እየተመለሰ በነበረበት ሰዓት የኦሮምያ ክልል የጸጥታ ኀይሎች ከሰንደቅ ዓላማ ጋር ተያይዞ ‹‹አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ያለበትን ነገር ያደረገና የያዘ ሰው አናሳልፍም›› በሚል በተፈጠረ ግጭት ከጸጥታ ኀይሎች በተተኮሱ ጥይቶች እና አስለቃሽ ጭስ ምክንያት በርከት ባሉ ሰዎች ላይ ጉዳት ደርሷል፡፡ በዚህም ምክንያት ሁለት ሰዎች በአለርት ሆስፒታል ሕክምና ሲደረግላቸው ቆይቶ በዛው ቀን ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን አንድ ግለሰብ ደግሞ ጥር ፲፫ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ሕይወቱ ማለፉን ኢሰመጉ አረጋግጧል” ብሏል በመግለጫው፡፡ የተፈጸመው ድርጊትና የደረሰው ጉዳት የዜጎችን ሰብአዊ መብት የሚጥስና የሕግ አግባብን ያልተከተለ በመሆኑ ድርጊቱን ማውገዙን ገልጿል፡፡

ከቤተ ክርስቲያን አካላት ጀምሮ በሀገር ውስጥ ያሉ የተለያዩ የፖለቲካ ኀይሎች ባወጧቸው መግለጫዎች ሥር እየሰደደ የመጣው ቤተ ክርስቲያንን ወደ ዳር የመግፋትና ወቅት ጠብቆ ጥቃት መፈጸም እየሰፋ መምጣቱን የሚያሳይ እና ለሀገር ህልውና ስጋት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ መንግሥት እንደመንግሥት የሀገሩን ዜጎች ሰብዓዊና መንፈሳዊ መብቶች የማክበር፤ በሀገር ውስጥ የሚኖሩ ሁሉምንም ዜጎች በእኩል ዓይን አይቶ የማስተዳደር እንዲሁም በደል ሲደርስ ፍትሕ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህም ባሻገር በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ተሰግሥገው ሀገር እንዳትረጋጋ በተለያየ አጋጣሚ ጠብ አጫሪ ድርጊቶችን በመፈጸም ኅብረተሰቡን ወደ አላስፈላጊ ድርጊት የሚገፉ ኀይሎችን ለይቶ በማውጣት ተገቢውን ቅጣት ሊሰጥ ይገባል፡፡ በጠቃላይ ከጥምቀት በዓል ጋር ተያይዞ በወይብላ ቅድስት ማርያም በበዐሉ ላይ ታድመው በነበሩ ምእመናን ላይ በተፈጸመው ኢሰብአዊ ድርጊት እንዲሁም በዕለቱ መግባት የነበረበት ታቦት ወደ መንበሩ እንዳይገባ የተደረገበትን መንገድ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች አውግዘዋል፡፡ በአጠቃላይ ከጥምቀት በዓል ጋርተያይዞ የወይብላ ቅድስት ማርያም ታቦት ወደ መንበሩ እንዳይመለስ በመደረጉ ምክንያት በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ የተገደደበትን መንገድ እንዲሁም በበዓሉ ላይ ታድመው በነበሩ ምእመናን ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ ድርጊትና ግድያ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች አውግዘውታል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥር ፲፭ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም  ባወጣው መግለጫ ድርጊቱን የፈጸሙ ወንጀለኞችን ለሕግ ለማቅረብ መንግሥት እየሠራ መሆኑን ማስታወቁ ይታወሳል፡፡

# ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከ፲፱፻፴ ዓ.ም- ፳፻፲፬ ዓ.ም

## . ብፁዕነታቸው በአገልግሎታቸው ትጉህ እና ለመንጋቸው እጅግ የሚጨነቁ አባት ነበሩ

ካሳሁን ለምለሙ

በቀድሞ ሸዋ ክፍለ ሀገር ፍቼ ዞን በሙከጡሪ ወረዳ በበቾ ፋኒሊ ቀበሌ ልዩ ስሙ ደሴ በሚባል ቦታ የተወለዱት፤ የቀድሞው መምህር ኃይለሚካኤል ወልደአምላክ ከ፳፻፱ ዓ/ም ጀምሮ ደግሞ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ተብለዋል:: ከመወለዳቸው አስቀድሞ ታላቅ ወንድማቸው በሞት ስለተለዩ እናታቸው ወይዘሮ በላየውነሽ በዲየ በጽኑ ሀዘን ላይ ወደቁ፤ ያን ጊዜም "ወንድ ልጅ ብትሰጠኝ ቃለ እግዚአብሔርን ተምሮ ቤትህን እንዲያገለግል እሰጣለሁ" በማለት ለእግዚአብሄር ስእለት ይሳላሉ:: ስእለታቸውም ተሰምቶ ወንድ ልጅ ወለዱ፤ በዚህ መሠረት ከእግዚአብሔር ያገኙትን ልጃቸውን በስምንት ዓመቱ ዘመኑን ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግል ዘንድ ሰጡ:: የስምንት ዓመት ዕድሜ የነበረው ታዳጊ ሕፃንም ወደ ትምህርት ቤት አመራ::



ብፁዕ አቡነ ሚካኤል

በወላጆቻቸው ፍቃድ በስምንት ዓመት ዕድሜያቸው ወደ ተማሪ ቤት ያመሩት መምህር ኃይለ ሚካኤል ከተለያዩ የአብነት ትምህርት ቤቶች የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ተከታትለዋል:: በጉባኤ ቤት ትምህርታቸውን እየቀጸሉ ባሉበት ወቅትም በድንገት ታመው ለሦስት ዓመታት ያህል በቤተሰቦቻቸው አስታማሚነት በህመም ላይ ቆይተዋል:: ባደረባቸው ህመም ምክንያት ከዚህ ቀደም በጉበኤ ቤቶች የተማሯቸውን ትምህርቶች በሙሉ ስለረሷቸው ጤናቸው ሙሉ መሻሻል ሲያገኝ እንደገና መጀመሪያ የተማሯቸውን ትምህርቶች ደግመው ተምረዋል:: ያቋረጡትን ትምህርት እየተማሩ በነበረበት ወቅትም ሌላ ፈተና መጣ፤ ይህም ሶማሊያ ኢትዮጵያን በኃይል በወረረችበት ወቅት ብሔራዊ ውትድርና (ዘመቻ) መሄድ ግድ ስለነበረ ይማሩበት ከነበረው የደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም ጉበኤ ቤት በቀጥታ ወደ ወታደር ማሰልጠኛ ተወሰዱ:: ከዚያም የተለያዩ ወታደራዊ ሥልጠና እየወሰዱ በነበረበት ወቅት በእድሜያቸው ምክንያት ተመልሰው እንዲመጡ ተደረገ:: ከሥልጠናው ከተመለሱ በኋላም ለመማር ይጓጉለት የነበረውን የአብነት ትምህርት ለመቀጸል ሁኔታዎች ተመቻቹላቸውና ያቆሙትን ትምህርት እንደገና ጀመሩ::

ሕይወታቸው በብዙ ውጣውረድና ፈተና የተሞላው እኒህ አባት ፈተናዎቹን ሁሉ በጽናትና በዓላማ በማለፍ ያሰቡትን ተምረው፣መድረስ የሚፈልጉበት ደረጃ ላይ ደርሰው ቤተ ክርስቲያንንና ሀገርን የሚጠቅም ዕውቀት ሸምተው ምሉዕ በኲልሄ የሆነ አገልግሎት ሲሰጡ ቀይተዋል:: በዕረፍተ ሥጋ እስከ ተለዩበት ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያንን ባስተማረቻቸው ትምህርት በዕውቀትና በተግባር በግለጥ በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው በፍጹም መንፈሳዊ ልጅነት ቤተ ክርቲያንን አገልግለዋታል:: ስለሆነም በቀድሞ መጠሪያቸው መምህር ኃይለሚካኤል ወልደአምላክ የአሁኑ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የዚህ ዕትም የቤተ አብርሃም እንግዳችን ናቸው:: መልካም ንባብ::

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ከአባታቸው ከአቶ ወልደ አምላክ ሁንዴና ከእናታቸው ከወ/ሮ በላይነሽ በዲየ በቀድሞ ሸዋ ክፍለ ሀገር ፍቼ ዞን በሙከጡሪ ወረዳ በበቾ ፋኒሊ ቀበሌ ልዩ ስሙ ደሴ በሚባል ቦታ በ፲፱፻፴ ዓ.ም ተወለዱ:: ብፁዕነታቸው መንፈሳዊ ትምህርት የጀመሩት በታላቁ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሲሆን በገዳሙ

ከሚገኙት ከአንጋፋው መምህር ገብረ ማርያም ንባብ ቤት መሠረታዊ የግእዝ ንባብ ተምረዋል። በደብረ ጽጌ ገዳም ደግሞ ከመምህር ልዑል ዘንድ የግብረ ዲቁና ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

**በሀገረ ስብከቱ በነበረው የአብያተ ክርስቲያናት አለመስፋፋት ችግር የተነሣ ምእመናን የመካነ መቃብር እጦትና መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማግኘት መቸገራቸውን የተረዱት ብፁዕነታቸው፤ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሃያ ሁለት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን የአብያተ ክርስቲያናት ቊጥር ወደ ሦስት መቶ ሰባ ሶስት አሳድገዋል።**

ከየኔታ መርዓዊ ዜና ደግሞ ከቃል ትምህርት ጀምረው ጾመ ድጓና ድጓ የተማሩ ሲሆን፤ ከመምህር ወልደ ገብርኤል ዝማሬ መዋሥዕት እንዲሁም ከአቋቋሙ መምህር ከየኔታ በትረ ማርያም ክብረ በዓል፣ መዝሙርና አርባዕት፣ ወርኀ በዓልና መኃትው፣ ስብሐተ ነግህና ኪዳን ሰላም፣ቅንዋትና አርያም ተምረዋል፤ በድጓሜም ዝማሬ መዋሥዕት በሚገባ ተምረው አጠናቅቀው በመምህርነት ተመርቀዋል።

በተጨማሪም ከመምህር ምሕረተ ሥላሴ ቅኔ ተምረው በድጋሜ ከመምህር ዐምዴ ጉባኤ ቤት ገብተው ለሁለተኛ ጊዜ ቅኔ ተቀኝተው ሙሉ አገባቡንም ቀጽለዋል። በታላቁ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመምህር ገብረ ኢየሱስ ስም በተሰየመው የብሉያትና ሐዲሳት ትርጓሜ አዳሪ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ትምህርታቸውን ለስምንት ዓመታት ተከታትለው ተመርቀዋል። ከዚያ በኋላም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ መልካም ፈቃድ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ምክትል መምህር በመሆን በታላቁ ደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተምረዋል። ብፁዕነታቸው ለመንፈሳዊ ትምህርት ካላቸው የተለየ ፍቅር የተነሣ የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ትምህርትን እያስተማሩ የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜና መጽሐፍተ ሊቃውንት በዚሁ ገዳም ተምረው ተመርቀዋል።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል የአበውን ፍኖት በመከተል ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፺፮ ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም ሥርዓተ ምንኵስናን ከፈጸሙ በኋላ በ፲፱፺፯ ዓ.ም ደግሞ በወቅቱ የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት ከብፁዕ አቡነ ዮሴፍ ዘንድ መዐርገ ቅስናን ተቀብለዋል። ብፁዕነታቸው መንፈሳዊ ትምህርት ለመቅሰም ከነበራቸው ትጋት ባልተናነሰ መልኩ በአገልግሎታቸውም እጅግ ትጉህ፣ ምስጉንና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አባት ነበሩ። ከሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ጥቂቱን ስንመለከት፡- በፍቼ ሀገረ ስብከት በስብከተ ወንጌልና ትምህርት ክፍል ሓላፊነት፤ በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም ባሉ የአብነት ጉባኤ ቤቶች ለተወጣጡ ሦስት መቶ ደቀ መዛሙርት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና በመሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ዙሪያ ተከታታይ ሥልጠና ሰጥተዋል፤ በመንፈሳዊ የትምህርት መስክ ያላቸውን መክሊት ከግንዛቤ በማስገባት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ምልካም ፈቃድ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ተመድበው እንዲያስተምሩ ታጭተው የነበረ፤ ቢሆንም የደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም አባቶችና ደቀ መዛሙርት በገዳሙ እንዲቆዩላቸው በጠየቁት

መሠረት በገዳሙ ቆይተው በመምህራቸው በመምህር ጥበቡ አስናቀ እግር ተተክተው ከ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ በዋና መምህርነት አገልግለዋል፡፡

የብፁዕ አቡነ ሚካኤልን አገልግሎት፣ የትምህርት ዝግጅትና መንፈሳዊ ሕይወት ተመልክቶ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ግንቦት ፲ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም ባደረገው ምልአተ ጉባኤ መሠረት የኢሊባቡር ሀገረ ስብከተ ኤጲስ ቆጶስ ሆነው እንዲሠሩ መርጧቸው ሐምሌ ፱ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አንብሮተ እድ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከሌሎች ዐሥራ አራት አባቶች ጋር ሥርዓተ ሢመታቸው ተከናውኗል፡፡

ብፁዕነታቸው በአገልግሎታቸው ትጉህና ለመንጋቸው እጅግ የሚጨነቁ ለመሆናቸው በተመደቡበት የኢሊባቡር ሀገረ ስብከት የሠሯቸው ሥራዎች ለስማቸው ሐውልት ሆነው የሚመሰክሩ ተግባራት ሆነዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል በሀገረ ስብከቱ ረጅም ዘመናትን ያስቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳደስ ለአገልግሎት ምቹ አድርገዋል፤ በተጨማሪም ማኅበረ ምእመናንን እና በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ዐሥራ አራት የሚሆኑ ታላላቅ ካቴድራሎችንና አድባራት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሳንጸዋል፡፡ በሀገረ ስብከቱ በነበረው የአብያተ ክርስቲያናት አለመስፋፋት ችግር የተነሣ ምእመናን የመካነ መቃብር እጦትና መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማግኘት መቸገራቸውን የተረዱት ብፁዕነታቸው፤ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ሃያ ሁለት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በመትከል በሀገረ ስብከቱ የሚገኙትን የአብያተ ክርስቲያናት ቍጥር ወደ ሦስት መቶ ሰባ ሶስት አሳድገዋል፡፡

ብፁዕነታቸው በሀገረ ስብከቱ ያለውን የአገልጋይ ካህናት እጥረት እና የስብከተ ወንጌል ውስን የሆነ ተደራሽነትንም መቅረፍ ዐቢይ ዓላማ በማድረግ በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር በመቱ ፈለገ ሕይወት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም እና ካህናት ማሰልጠኛ ማዕከል የአብነት ትምህርት ቤት በማቋቋም ከየወረዳው የተወጣጡ አርባ ስድስት ደቀ መዛሙርት እንዲማሩ አድርገዋል፡፡ በሀገረ ስብከቱ ላሉ ምእመናን ወንጌልን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው (በአፋን ኦሮሞ) ተደራሽ ለማድረግ አይነተኛ መፍትሔ መሆኑን የተረዱት ብፁዕነታቸው፤ የካህናት ማሰልጠኛዎች እንዲጠናከሩ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሠርተዋል፡፡ ከካህናት ማሠልጠኛው በተጨማሪ ሀገረ ስብከቱን በገቢ ለማጠናከር ግምቱ ከሰማንያ ሚሊየን ብር በላይ የሚገመት ዘመናዊ ባለ አምስት ፎቅ ሁለገብ ሕንጻ በማሳነጽ ላይ ነበሩ፡፡ ብጹዕ አቡነ ሚካኤል የመጻሕፍት ሊቅ መሆናቸውና በትምህርት መስፋፋት ላይ በርትተው መሥራትን የሚመርጡ አባት ስለነበሩ የካህናት ማሠልጠኛን ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅ ለማሳደግ የሕንፃ ግንባታ አስጀምረዋል፡፡

ምእመናን በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርት በሁለት በኩል የተሳሉ ሰይፍ እንዲሆኑ በማሰብ የአጸደ ሕጻናት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በማሳነጽ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲቀጥል አድርገዋል፡፡ የሀገረ ስብከቱን ገቢ ለማሳደግ በመቱ ከተማ ሁለት ተጨማሪ ሕንጻዎችን አስገንብተዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን መገለጫ የሆነውን የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ከግምት ውስጥ በማስገባት የመናፈሻ ሥፍራዎችን በመቱ ከተማ የማደራጀት ሥራዎች ሠርተዋል፡፡ ብጹዕ አቡነ ሚካኤል ሀገራችን ኢትዮጵያ በገጠማት የሰላም እጦት ወቅት በሀገረ ስብከታቸው ባሉ አድባራትና ገዳማት ጸሎተ ምህላ እንዲደርስ በማድረግ የሰላም ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሰላምን ይሰጥ ዘንድ ሲጸልዩ ቆይተዋል፡፡

ብጹዕ አቡነ ሚካኤል በሠሯቸው ሥራቸው ብዙ የሚነገርላቸው፣ እጅግ መንፈሳዊና ተሐራሚ የሆኑት ሲሆኑ ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን መክሊት በብዙ አትርፈው በአደረባቸው ህመም ምክንያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ጥር ፱ ቀን ፳፻፳፬ ዓ.ም. በሃምሳ አራት ዓመታቸው በዕረፍተ ሥጋ ተለይተዋል፡፡ የቀብር ሥነ ሥርዓታቸውም ጥር ፲፯ ቀን ፳፻፳፬ ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፣ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሓላፊዎች፣ የኢሊባቡር ሀገረ ስብከት ሓላፊዎችና ምእመናን በተገኙበት በደብረ ሊባኖስ አንድነት ገዳም ተፈጽሟል፡፡ እግዚአብሔር አምላካችን የብፁዕ አባታችንን ነፍስ ለወዳጆቹ ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ባዘጋጀው መካነ ዕረፍት በክብር ያሳርፍልን፣ እኛን የመንፍስ ቅዱስ ልጆቻቸውንም ያጽናን፤ በረከታቸውንም በላያችን ያሳርፍልን፡፡ አሜን፡፡

የብፁዕ አቡነ ሚካኤል የትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት በታህሣሥ ወር ፳፻፳ ዓ.ም በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ መውጣቱ ይታወሳል፡፡

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# «የሕክምና ባለሞያዎች ተገልጋይ ወገኖቻችንን በእጅጉ ደስ ያሰኘ አገልግሎት መስጠት ችለናል»

ሲስተር ዘነበች ቆርቾ

በምኒልክ ብርሃኑ

በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እና በአገራችን በኢትዮጵያ በየዘመናቱ በተነሡ ዓላውያን ነገሥታት እና ጠላቶች የደረሱትን ጥፋቶች ለመዘርዘር እስካሁን የተጻፉት ድርሳናት በቂ አይደሉም። እልቂቶቹ እና ጥፋቶቹ ከፍተኛ በመሆናቸው የማይተካ የሰው ልጆችን ነፍስ ከመንጠቅ ጀምሮ የማይመለሱ ቅርሶችን አውድሟል። ነገር ግን ቁሳዊ ጉዳትን ከማድረግ በስተቀር ሰማያዊውን ሃይማኖትን እና ዐሥራት አገራችንን ኢትዮጵያን ሊያወድማት አልቻለም። ይልቁንም አንድነትን በማጠናከር ወደ ፊት እንዲቀጥል የተኛን ልቡና መቀስቀስ ችሏል። በእንደነዚህ ዓይነት ጊዜያትም ከጠላቶቿ በላይ ዕንቍ ልጆቿ ይበልጥ እንዲደምቁና እንዲያበሩ አድርጓቸዋል።

በሰሜኑ በተከሠተው የአገራችን ጦርነት በቤተ ክርስቲያን እና በሕዝባችን ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። ነገር ግን ቀውሱ ተባብሶ የከፋ ደረጃ ከመድረሱ አስቀድሞ እንደ ቀደሙ አባቶች ከመሣርያ አፈ ሙዝ ጋር በመጋፈጥ እንዳይባባስ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዳይቋረጡ፣ ሰዎች ጦርነቱ ከፈጠረባቸው ጉዳት በላይ ሥነ ልቡናዊ ቀውስ ውስጥ እንዳይቀሩ ከግለሰብ እስከ ተቋማት ድረስ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርጉ የነበሩ አሉ።

መዝሙኛው ቅዱስ ዳዊት "በጎውን ማን ያሳየናል የሚሉ ብዙ ናቸው" (መዝ ፬፥፮) ሲል አስቀድሞ እንደተናገረው በዚህ አስከፊ ጊዜ አርአያ የሚሆን ተግባር የፈጸሙ ቅዱሳን አባቶች፣ መንፈሳዊ ተቋማት ግለሰቦች በርካቶች ናቸው። በዛሬው ቆይታችን ችግር ያፋቀራቸው፣ መከራ ያሰባሰባቸው፣ ለሁለት ወራት በጦርነት ቀጠና ውስጥ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ኅብረተሰብን ሲያገለግሉ የነበሩ በማኅበረ ቅዱሳን የደሴ ማዕከል አገልጋዮችን ልናቀርብላችሁ ወደድን። በዚህ የጦርነት ወቅት የደሴ ማዕከል ዘመን በማይፍቀው ድርሳን ላይ ታሪካቸውን አኑረዋል።

የመንግሥትና የግል ጤና ተቋማት ከጥቅምት ወር ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ በጦርነቱ ምክንያት አገልግሎት መስጠታቸውን አቋርጠው ነበር። ይሁን እንጂ የጤና ባለሞያዎች ባደረጉት ድጋፍ አገልግሎቱ እንዲቀጥል ተደርጓል። እኛም ከዋና ማዕከላችን አዲስ አበባ ተነሥተን ወደ ደሴ በማቅናት የጤና ባለሞያዎች አስተባባሪ ከሆኑት ሲስተር ዘነበች ጋር ቃለ መጠይቅ አድርገናል። ይህንን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተባበሩን ዲያቆን አሻግሬ አምጤ እያመሰገንን፤ ያደረጉትን ቃለ መጥይቅ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል። መልካም ንባብ!

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስለሆኑ በዝግጅት ክፍላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን። በቅድሚያ ራስዎን፣ የሚሠሩበትን ተቋም እና በማኅበረ ቅዱሳን ያለዎትን የአገልግሎት ድርሻዎ በማስተዋወቅ ቆይታችንን ብንጀምር፤**

**ሲስተር ዘነበች፡-** ሲስተር ዘነበች ቆርቾ እባላለሁ፤ የደሴ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህርት ነኝ። በማኅበረ ቅዱሳን አገልግሎት ደግሞ በደሴ ማዕከል ግቢ ጉባኤያት ማስተባበሪያ ክፍል ውስጥ እያገለገልሁ እገኛለሁ። በአጥቢያችን በደብረ ቤቴል ቅድስት ሥላሴ እና ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ደግሞ በስብከተ ወንጌል ክፍል አገለግላለሁ፤ እንዲሁም በጦርነቱ ወቅት የጤና ባለሞያዎች አስተባባሪ በመሆን ስሠራ ቆይቻለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ደሴ ከተማ የጦርነት ቀጠና ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ማኅበራዊ ቀውሶች ተፈጥረዋል፤ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ማኅበራዊ ቀውሶች ተባብሰው የከፋ ችግር እንዳይፈጠር በተለይም በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ርብርብ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይህ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? የእርስዎ ድርሻስ ምንድን ነበር?**



ሲስተር ዘነበች ቆርቾ

**ሲስተር ዘነበች፡-** ጦርነቱ ደሴ ከተማ በደረሰ ጊዜ ሁኔታዎች በጣም አስፈሪ እና አሳሳቢ ነበሩ። ማኅበራዊ አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ቆመዋል። ሕዝቡም ጦርነቱ ከፈጠረበት ሥጋት በተጨማሪ እነዚህ ተቋማት በመቋረጣቸው ከፍተኛ ችግር ውስጥ ወድቆ ነበር። በተለይ እንደ አገር የጤናው ዘርፍ ለኅብረተሰቡ የሚሰጠው አገልግሎት የተዳከመ በመሆኑ ይህ ሲጨመርበት ደግሞ የተፈጠረው ቀውስ ከባድ ነበር። በዚህ ሁኔታ ሳለን በሃይማኖት አባቶች፣ በተለይም ደግሞ የደቡብ ወሎና በኦሮሞ ብሔረሰብ የከሚሴ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ አሳሳቢነት እናቶችና ሕፃናት እንዳይሞቱ እና የጤናው ችግር የበለጠ እንዳይባባስ የሕክምና ባለሞያዎችን አሰባስባችሁ ርዱ የሚል ጥሪ ቀረበ። በዋናነት በማኅበረ ቅዱሳን የደሴ ማዕከል

ይህንን የብፁዕ አባታችንን ጥሪ በመቀበል ባለሞያዎችን የመሰብሰብ እና የማስተባበር ኃላፊነቱን ወስዶ አስተላለፈ:: ለኅብረተሰቡም በተለያየ መንገድ መረጃው ተደራሽ እንዲሆን ተደረገ:: በዚህ መሠረት በደሴ ከተማ የሚገኙ በርካታ የጤና ባለሞያዎች ተሰባስበው የጤና አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተደረገ:: እኔ ደግሞ የዚህ ኮሚቴ አስተባባሪ በመሆን ተመረጥሁ:: ይህ የተደራጀው የጤና አስተባባሪ ኮሚቴ የደሴ ከተማ ሰላምና መረጋጋት ክፍል ዕውቅናና ፈቃድ እንዲሰጠው ካደረግን በኋላ የተቋረጠው አገልግሎቱ እንዲቀጥል እንቅስቃሴዎች ተጀመሩ:: በመሆኑም በከተማ በሚገኙ ጤና ጣቢያዎች እና በደሴ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የሕክምና ድጋፍ ሲደረግ ቆይቷል፤ በዚህም መልካም ሥራ ተሠርቷል::

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጤና አስተባባሪው ኮሚቴ ሥር የነበሩ አባላት የጤና ባለሞያዎች ብቻ ነበሩ? ሌሎች አካላትስ ተስፏቸው እንደምን ነበር?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** በጦርነቱ አለመረጋጋት ምክንያት በደሴ ከተማ የሚገኙ የመንግሥት እና የግል ጤና ተቋማት ከጥቅምት ወር ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎታቸውን አቋርጠው ስለነበር ኪሚቴው በእነዚህ ተቋማት ውስጥ ሲሠሩ የነበሩ ባለሞያዎች እንዲካተቱ ተደርጓል:: ከጤና ተቋማቱ ውጭ የሚሠሩ የጤና ባለሞያዎች፤ የዩኒቨርሲቲዎችና የጤና ሳይንስ ኮሌጆች ሠልጣኞች እና ልዩ ልዩ በጎ ፈቃደኞ (ወጣቶች፣ ጎልማሶች፣ አረጋውያን፣ መነኮሳይያትና መነኮሳት፣ የየጤና ተቋማቱ የአስተዳደር ሠራተኞች) በማስተባበር አገልግሎቱ እንዲቀጥል አድርገዋል:: የሃይማኖት አባቶችም በየጤና ተቋማቱ በአካል በመገኘት በምክርና በማበረታታት የማይተካ ሚና አበርክተዋል::

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ የተጎዱ፣ ጊዜ በማይሰጥ ሕመም የታመሙ፣ ነፍሰ ጡር እና አራስ እናቶች፣ ተመላላሽ ታካሚዎች፣ በርካታ ሕመምተኞች እንደ ነበሩ ይታወቃል:: ለእነዚህ ሁሉ ሕመምተኞች በበቂ ሁኔታ የሕክምና ቁሳቁሶች ነበሩ?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** የሃይማኖት አባቶች ጥሪ ሲያደርጉ የመገናኛ እና የመጓጓዣ አውታሮች ባለመኖራቸው ሌሎች ቦታዎች ምን እንደተፈጠሩ እና ምን ምን ነገሮች እንዳሉ መረጃዎች ቀድመው አልነበሩንም:: ካለምንም ቅድመ ሁኔታ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ጥሪውን ተቀብለን ወደ ፊት ሔድን:: ጥሪ የተደረገበት ቦታ ስንሄድ ግን በቂ የሕክምና ቍሳቍሶች እና የመድኃኒት አቅርቦቶች አልነበሩም፤ የቀሩት የሕክምና ቍሳቍሶች እና መድኃኒቶችም ተዘርፈዋል:: ካለ መድኃኒት ደግሞ ሕክምና ማድረግ ስለማይቻል ቀዳሚ ሥራችን የሆነው ግብዓት ማሰባሰብ ነው:: ስለዚህ መድኃኒቶችን ከግል ጤና ተቋማትና ከበጎ ፈቃደኞች ሰበሰብን፤ ከዚያም የሰበሰብናቸውን መድኃኒቶች ከሃይማኖት አባቶች ጋር በመመካከር በወራሪው ኃይል እንዳይዘረፉ በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ በሥውር ሥፍራ እንዲቀመጡ አደረግን:: በጣም የሚገርመው ደግሞ ከዘረፋ የተረፉ ንብረቶችንና የሕክምና መገልገያዎችን (ኦክስጂን ጨምሮ) በቤታቸው ደብቀው የነበሩ ግለሰቦች አምጥተው ሲሰጡን ተደንቀናል:: በአጠቃላይ ይህንን መነሻ አድርገን ሕክምና መስጠት ጀመርን::

**ስምዐ ጽድቅ፡- የተሰጡት የሕክምና አገልግሎቶች ምን ምን ናቸው?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** ወደ ሥራችን ከመግባታችን በፊት በጦርነት ጊዜ በጣም የሚያስጨንቁ እና ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅድሚያ ሕክምና የሚያስፈልጋቸውን የሕመም ዓይነቶችን ነው የለየነው:: ከእነዚህ መካከልም የወሊድ አገልግሎት በዋናነት ይጠቀሳል:: በዚህም መሠረት ቀንና ሌሊት፣ ቅዳሜና እሑድን ጨምሮ ፹፩ እናቶችን የማዋለድ አገልግሎት በመስጠት ካለምንም ችግር በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት በሰላም ለመገላገል ችለዋል:: የሕክምናውም ድጋፍ በጤና ጣቢያዎች ብቻ የተወሰነ ባለመሆኑ ዐሥር እናቶች በየቤቱ በተደረገው ድጋፍ እና ክትትል ወልደዋል:: የስኳርና የደም ግፊት፤ የኤች አይ ቪ ኤድስ እና የአእምሮ ሕሙማን፤ አጠቃላይ ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ፤ መድኃኒት ያስፈልጋቸው የነበሩ ሰዎችን ጭምር መርዳት ተችሏል:: የቍስል ሕክምና፣ ጥይት ለማውጣት የተደረገ ቀላል ቀዶ ሕክምና፣ ቍስል ማጽዳትና መንከባከብ ፤ በአጠቃላይ ኅብረተሰቡን ጨምሮ በጦርነቱ ለቈሰሉ ለመከላከያ ሠራዊት አባላት፣ ለልዩ ኃይሎችን እና ለሲቪል ማኅበረሰቦች ሕክምና ተሰጥቷል::

የሃይማኖት አባቶችም በየጤና ተቋማቱ በመገኘት፣ ምክር በመስጠት እና በማበረታታት የጤናውን አገልግሎት የሚያውኩ ነገሮችን በመቀነስ የማይተካ ሚና አበርክተዋል:: የሕክምና ባለሞያዎችም ካለምንም መታከት እና ድካም ሲሠሩ ቆይተዋል:: ምንም እንኳን የጤና ሞያ የቡድን ሥራ ቢሆንም፤ ለዚህ የበረከት ጥሪ መልስ በመስጠት በግለሰብ ደረጃ በየቤቱ እየዞሩ በከፍተኛ ትጋት ሕክምና ሲሰጡ፣ ሲያዋልዱ እና ድጋፍ ሲያደርጉ የቈዩ ነርሶች ነበሩ:: ከጤና ባለሞያዎች ተጨማሪም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች ስለ ሕክምና ሁኔታ ከታካሚዎች መረጃ በመቀበል ለጤና ባለሞያዎች በማቀበል፤ ንብረቶችን ከዘረፋ በመጠበቅ፤ የቈሰለን አካል ለመስፋት እንዲያመች ጠጉሩን መላጨት፤ ለሕክምናና እንክብካቤ እንዲያመች በቁስለኞች ራስጌ ላይ ስማቸውን፣ የጉዳቱን ዓይነት፣ ቍስል የሚቀየርበትን ጊዜ፣ የሚወስዱትን የመድኃኒት ዓይነት ጽፎ በመለጠፍ፤ የተጎዳን አካል ድጋፋዊ ልምምድ እንዲያደርግ በመርዳት፤ በሞት የተለዩትን በመገነዝ እና በመቅበር፤ የቍስለኞችን መረጃ ለቀይ መስቀል እና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት በማሳወቅ ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል:: በዚህም ሊመሰገኑ ይገባል::

**ስምዐ ጽድቅ፡- በማኅበረ ቅዱሳን የደሴ ማዕከል የነበረውን ድርሻ እንዴት ይገልጹታል?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** በዚህ የጦርነት ጊዜ ማኅበረ ቅዱሳን አርአያነት ያለው ተግባር ነው ሲፈጽም የቆየው:: መጀመሪያ ጥሪው ከቤተ ክርስቲያን ሲተላለፍ በእግር በየቤቱ በመዞር መረጃውን የጤና ባለሞያሞች እንዲሰሙ አድርጓል:: ባደረጋቸው እገዛዎች የእናቶችና የሕፃናትን ሞት በመቀነስ፣ የጤና ጉዳቶች በመቀነስ፣

የኅብረተሰቡን ጭንቀት በመቀነስ፣ የሕክምና አቅርቦቶች እንዳይጓደሉ በማድረግ፣ መድኃኒቶችን በማሰባሰብ፣ አባላቱ ከኪሳቸው ጭምር ገንዘብ በማውጣት መድኃኒቶችን በመግዛት እና በማስተባበር የአንበሳውን ድርሻ ወስዷል ማለት እንችላለን።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ጦርነት በባሕሪው ከሚፈጥረው ቍሳዊ ኪሣራ እና አካላዊ ጉዳት በላይ ሥነ ልቡናዊ ስብራቱ ከፍተኛ ነው። ሥነ ልቡናዊ ስብራት ከመጠገን አንጻር ምን ተሠርቷ? እንደዚህ ዐይነት ችግሮች ሲከሠቱ ከማኅበረሰቡስ ምን ይጠበቃል?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** በዚያ የጦርነት ሰዓት ብዙዎቻችን ጭንቅ ውስጥ ነበርን። ለከፋ ሥቃይ እና ኀዘን የተዳረጉ፤ ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው፤ ከአንድ ቤተሰብ ሁለት ሦስት ልጆች በመሣሪያ ተመትተው የሞቱባቸው ወገኖቻችን ነበሩ። ነፍሰ ጡር የሆኑ ሴቶች እርግዝና ከሚያመጣው ጭንቀት በተጨማሪ ጦርነቱ የሚፈጥርባቸው ጫና እጅግ ከባድ ነበር። እኛ ከመድረሳችን በፊት የወለዱ እናቶች ይህ ጊዜ መቼ ነው የሚያልፈው የሚለው ያስጨንቃቸው ነበር። እነዚህ ሁሉ ከአካላዊ ሕክምና በላይ ሥነ ልቡናዊ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ናቸው። ጦርነቱ ደግሞ ብዙ ቤተሰቦችን አለያይቷል፤ ከአካላዊ ጉዳት በላይ ሥነ ልቡናዊ ስብራት የሚመጣው ደግሞ ብቻዬን ነኝ፣ ደጋፊ፣ ጠያቂ የለኝም ከሚል ስሜት የሚመጣ በመሆኑ ወገን እንዳላቸው እንዲሰማቸው ለማድረግ ብዙ ጥረት አድርገናል። በተለይም ማኅበረ ቅዱሳን ደሴ ማዕከል በጤናው ዘርፍ ላለነው ባለሞያዎች የተሰጠን ተልእኮ ወገኖቻችንን የማጽናናት እና የማረጋጋት ሥራ ነው። በዚህ መሠረት በየጊዜው ከሃይማኖት አባቶች ጋር እየሄድን የማስተማር እና በእግዚአብሔር ቃል የማጽናናት ሥራዎች ተሠርተዋል። በተደጋጋሚ አለንላችሁ በማለት እናበረታቸውም ነበር። እኛን ሲያገኙን በጣም ደስ ብሏቸው "ሰው አለን ማለት ነው" ይሉን ነበር።

በተለይ በሆስፒታል እና በጤና ጣቢያዎች ተኝተው የነበሩ ታካሚዎችን የቤተሰብ ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ ገላቸውን ማጠብ፣ አልጋ ላይ እንዳሉ ማገላበጥ፣ ዳያፐር መቀየር፣ ምግብ መመገብ እና ጠጉራቸውን መላጨት ተችሏል። እንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች በሚከሠቱ ጊዜ ትልቁ ሥራ የልቡና ጉዳቱ ዘላቂነት እንዳይኖረው ማድረግ ነው። ስለዚህ ሁላችንም ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ማኅበረሰብ፤ የሃይማኖት እና የመንግሥት ተቋማት ይመለከተናል ማለት ነው። የከፋ ቀውስ እና ጉዳት ከመድረሱ በፊት በተፋጠነ መልኩ ርዳታ ማድረግ እንዲቻል የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የድንገተኛ አደጋ ጊዜ እቅድ ያስፈልጋቸዋል። እዚህ ላይ በደንብ ቢሠራ መልካም ነው እላለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነት ጊዜ በፈቃደኝነት ኅብረተሰብን ለማገልገል መነሣት የውስጥ ጥንካሬን ይጠይቃል፤ እርስዎ እና ሌሎች የሞያ ባልደረባዎችዎ ይህንን ልበ ሙሉነት እንዴት አገኛችሁት?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** በጦርነት ቀጠና ውስጥ ሆኖ ለማገልገል መነሣት ቆራጥነትን ይጠይቃል። ምንድን ነው የሚገጥመኝ በሎ ማሰብ፣ ምን ሊፈጠር ይችላል ብሎ መጨነቅ አለ። ሆኖም፣ ጥሪው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን እና እንደ አንድ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ምንም ነገር ቢመጣ ራስን ለመሥዕትነት ማዘጋጀት ያስፈልጋል። እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ደግሞ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ነው የአገርን ፍቅር ለመግለጽ ዕድሉ የሚገኘው። በዚህ ስሜት ውስጥ ሆነን ነው ለማገልገል የተነሣነው። የሃይማኖት አባቶችም "በርቱ! ከጐናችሁ አለን፣ እንዳትፈሩ፤ ምንም ነገር ቢፈጠር ከእናንተ ጋር ነን" እያሉ ያበረቱን ስለነበር በልበ ሙልነት ወደ ፊት እየገፋን ሄድን። ባሳለፍናቸው ጊዜያት አባቶቻችን ከጎናችን ነበሩ፤ ከእነርሱ ጋር ሆነን የሚመጣ ነገር ካለ አብሮ ለመቀበል ተዘጋጅተን ወደ ሥራ ገባን። እንደ ባለሞያ ደግሞ በኢትዮጵያ የጤና ዘርፍ ሥርዓት ውስጥ "ርኅራኄ፤ አርአያነት፤ አለማድላት፤ ቅንነት፤ ትብብር.... ወዘተ" የሚባሉ ቁልፍ ዕሴቶች አሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እነዚህን የጤናው ዘርፍ ቁልፍ ዕሴቶች ማስቀደምና መተግበር ግዴታ ነው። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ እነዚህን ተግባራዊ አድርገናል። ቀን እና ሌሊት፤ ቅዳሜ እና እሑድም ካለ ምን ዕረፍት ለማገልገል ችለናል። እዚህ ጋር ስሟን ሳላነሣ የማላልፋት እስከዳር የምትባል አዋልጅ ሐኪም ነበረች። ይቺህ ሐኪም በማንኛውም ሰዓት ስትፈለግ የምትገኝ፤ በዛ አስጨናቂ ወቅት ሌሊት ምጥ የመጣባቸው እናቶችን ታዋልድ ነበር። ማንንም ሳትፈራ ደሴን ከተማ ብቻዋን በእግር እየዞረች ድጋፍ ታደርግ ነበር።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻም ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

ሲስተር ዘነበች፡- ከዚህ ጦርነት የተማርነው ትልቁ ነገር የሃይማኖት ተቋማት በሰላሙ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በእንደዚህ ዐይነት ወቅቶችም የማይናቅ ሚና እንዳላቸው ነው። እንደሚታወቀው በአገራችን ያለው የሕክምና አሰጣጥ ወደ ኋላ ከመቅረቱም በላይ በተደጋጋሚ ጊዜ በሚፈጠሩት ቀውሶች ዘርፉን ከማዘመን ይልቅ እንዳያድግ አድርገውታል። ስለዚህ የጤናው ዘርፍ የተሻለ ለውጥ እና ውጤት ለማምጣት የሃይማኖት ተቋማትን በዘላቂነት መጠቀም ቢቻል ብዙ ነገሮችን ማሳካት እንችላለን ብዬ አምናለሁ። በተጨማሪው አሁን ያ የጭንቅ ጊዜ አልፎ ለዚህ በመብቃታችን እግዚአብሔርን በጣም አመሰግነዋለሁ። ምክንያቱም መቼ ይሆን ይህ የጭንቅ ጊዜ የሚያልፈው? መቼ ነው ከዚህ ነገር የምንወጣው? የሚል ጥያቄ ሁሉም ነበረው። ሁሉም ነገር የተለመደ ሕይወት አልነበረም፤ ወደ አልተለመደ ሕይወት ውስጥ ነው የገባነው። እስከመቼ ነው የሚቀጥለው የሚለው ነገር ያስጨንቃል። ያ ሁሉ አልፎ እነዚህ የሰቀቀን ጊዜያት በመውጣታችን እግዚአብሔር ይመስገን ዛሬ እዚህ ለመድረስ ችለናል። በአጠቃላይ የሕክምና ባለሞያዎች ወገንን በእጅጉ ያስደሰተ አገልግሎት ሰጥተናል ማለት ነው።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም እናመሰግናለን?**

**ሲስተር ዘነበች፡-** እኔም እዚህ ድረስ መጥታችሁ ቃለ መጠይቅ ስላደረጋችሁልኝ አመሰግናለሁ።

# አራቱ ዐበይት ነቢያት፤ ክፍል አንድ ነቢዩ ኢሳይያስ

ምኒልክ ብርሃኑ

ልጆች! እንደምን አላችሁ? የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን እኛ በጣም ደኅና ነን:: ትምህርት እንዴት እየሄደ ነው? አሁን የመጀመርያ መንፈቀ ዓመት ወይም አንደኛ ሴሚስተር አጠናቃችሁ የዕረፍት ጊዜ ላይ እንደሆናችሁ እናምናለን:: ታዲያ ልጆች! በዚህ የዕረፍት ጊዜችሁን ዝም ብላችሁ ማሳለፍ የለባችሁም:: ስለዚህ የሚጠቅማችሁን የተለያዩ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ማንበብ አለባችሁ:: ጎበዞች!!

ልጆች! ከመጽሐፍ ቅዱስ የነቢያት ክፍል ስለ ጸፉት ቅዱሳን ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ ለጓደኞቻችሁ ንገሩዋቸው:: መጽሐፍ ቅዱስን ከጻፉት ቅዱሳን መካከል ነቢያት ይጠቀሳሉ::

ነቢያት ትንቢት የሚናገሩ ቅዱሳን ናቸው:: ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ወደ ፊት የሚሆነውን ቀደም ብለው ይናገራሉ:: ታዲያ ልጆች! እነዚህ ነቢያት ከእግዚአብሔር ትእዛዝን ተቀብለው ለሕዝቡ ያስተላልፋሉ፤ በእግዚአብሔር ውሳኔ የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ይናገራሉ፤ በኃጢአት ምክንያት መንግሥታት እና ሰዎችን ይገሥጻሉ፤ ይቆጣሉ፤ ምክርም ይሰጣሉ::

ልጆች! ቅዱሳን ነቢያትም በሁለት የሚከፈሉ ሲሆን እነርሱም ዐበይት ነቢያት እና ደቂቅ ነቢያት ይባላሉ:: ዐበይት ነቢያት ደግሞ አራት ሲሆኑ ነቢዩ ኢሳይያስ፣ ነቢዩ ኤርምያስ፣ ነቢዩ ሕዝቅኤልና ነቢዩ ዳንኤል በመባል ይታወቃሉ:: ከዚህ በኋላ በተከታታይ ክፍል በቅደም ተከተል ስለአራቱ ዐበይት ነቢያት ታሪካቸውን፣ ማንነታቸውን እና መጻሕፍቶቻቸውን እናጠናለን ማለት ነው::

ልጆች! በዛሬው በክፍል አንድ ቆይታችን ቀድመን የምናጠናው ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ ነው:: ከዚህ በታች ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ ማንነት፣ ለነቢይነት እንዴት እንደተመረጠ እና ስላስተማረው ትምህርት፤ እንዲሁም ስለ ትንቢት መጽሐፉ እንማራለን:: ታሪኩን በጥሞና እንድትከታተሉ እንጋብዛለን::

ልጆች! ኢሳይያስ ማለት መድኃኒት ወይም ድኅነት ማለት ነው:: አባቱ አሞጽ፤ እናቱ ሰፊያ ይባላሉ:: በኢየሩሳሌም ሀገር ከሚስቱ እና ሁለት ልጆች ጋር አብሮ ይኖር ነበር:: በኢየሩሳሌም ሀገር በቤተ መንግሥት ውስጥ የንጉሥ አማካሪ ሆኖ በሚያገኘው ገንዘብ ቤተሰቦቹን እያስተዳደረ ይኖር ነበር:: በሥራውም ምክንያት በቤተ መንግሥት በፍርድ ዐደባባይ አይታጣም ነበር::

ታዲያ ልጆች! ነቢዩ ኢሳይያስ በኢየሩሳሌም ሀገር ሲኖር በእርሱ ዘመን በየጊዜያቸው የነገሡ ያዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝ እና ሕዝቅያስ የሚባሉ የይሁዳ ነገሥታት ነበሩ:: ከአራቱ መካከል በጣም የሚወደውና ጓደኛው ንጉሥ ያዝያንን ነበር::

ከዕለታት ባንድ ቀን ንጉሥ ያዝያን ሥልጣኑን ተጠቅሞ የክህነት አገልግሎት እሰጣለሁ ብሎ በድፍረት ተነሣ:: ኢሳይያስ ደግሞ ያዝያን በጣም የሚወደው ጓደኛው በመሆኑ ድርጊቱን አይቶ ሳይቆጣው ዝም አለው:: በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ኢሳይያስ ላይ ተቆጣ፤ በከንፈሩ ላይ ቁስል አወጣበት:: ጓደኛው ንጉሥ ያዝያንም ሞተ::

ከብዙ ጊዜ በኋላ እግዚአብሔር በረጅምና ከፍ ባለ በሚያስፈራ ዙፋን ላይ ሆኖ ለኢሳይያስ ተገለጠለትና አናገረው:: ኢሳይያስም "አጥፍቻለሁና ወዮልኝ" ብሎ በፊቱ ሰገደ፤ በሥራውም ተፀፀተ:: እግዚአብሔርም መልአኩን ልኮ ከንፈሩን አዳነው:: ከዚህም በኋላ ለነቢይነት ተመረጠ::

ልጆች! ነቢዩ ኢሳይያስ ለነቢይነት ከተመረጠ በኋላ ትንቢት እየተናገረ፣ ሕዝቡን እያስተማረና እየመከረ ከ፶፪ ዓመት በላይ አገልግሏል። የጻፈው መጽሐፍ ደግሞ ትንቢተ ኢሳይያስ ይባላል። ትንቢተ ኢሳይያስ በ፷፮ ምዕራፎች የተከፋፈለና ፲፪፻፴፩ (1231) ቁጥሮች አሉት። በዚህ የትንቢት መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተላለፉ ሰዎች እንደሚቀጡ፣ ዐመጸኞች ነገሥታትን እንደሚያጠፋቸው፣ የራሱ የሆኑትን ሕዝብ ግን እንደሚያድናቸው፤ እግዚአብሔር ስለሚወደው እውነተኛ አምልኮ፣ ጾም፣ የሰንበት አከባበርን ወዘተ. ያስተምራል።



ነቢዩ ኢሳይያስ ለነቢይነት እንደተመረጠ

ልጆች! ነቢዩ ኢሳይያስ በጣም የሚታወቅበት ታላቅ ትንቢት አለ። ይኸውም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችን መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷን ቀድሞ በመተንበዩ ነው።

ከብዙ ጊዜ በኋላ በኢየሩሳሌም ሀገር ምናሴ የሚባል ንጉሥ ነገሠ። ታዲያ ልጆች! ይኽ ንጉሥ የጣዖት ምስል በማቆም ያመልክ ጀመር፤ ሕዝቡም እግዚአብሔርን በመተው ንጉሡ ላቆመው ጣዖት መስገድ ጀመሩ። በኋላ ነቢዩ ኢሳይያስ ከመጥፎ ሥራቸው እንዲመለሱ፤ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲጠብቁ አስተማራቸው። እነርሱ ግን ሊመለሱ አልቻሉም።

ከዚያም ኢሳይያስ በድጋሜ ወደ ንጉሡ ሄደና ለጣዖት ሳይሆን ለእግዚአብሔር መስገድ እንዳለበት ነገረው። ንጉሡ ግን እንዴት በድፍረት ይናገረኛል ብሎ ተቆጣ። ከክፉ ተግባሩ ከመመለስ ይልቅ ኢሳይያስን ሊቀጣው ፈለገ፤ ቶሎ ብሎ ወታደሮቹን አስጠርቶ በመጋዝ እንደሚቆራርጡት አዘዘ። እነርሱም ንጉሡ እንደአዘዛቸው አደረጉ። ነቢዩ ኢሳይያስም መስከረም ፮ ቀን ዐረፈ። ከዚህ በኋላ በየዓመቱ መታሰቢያ ይደረግለታል።

አያችሁ አይደል የንጉሥ ምናሴን ሥራ! እግዚአብሔር አምላክህን ብቻ አምልክ የሚለውን ቃል ትቶ ጣዖት ማምለክ ጀመረ። በዛም ላይ ነቢዩ ኢሳይያስ ተው ሲለው ለምን ተናገርከኝ ብሎ አስገደለው። በዚህም ጥፋቱ እግዚአብሔር ቀጣው ኢየሩሳሌምም በጠላት ተወረረች።

ልጆች! ከዚህ ታሪክ የምንማረው በመጀመሪያ ማንም ሰው ጥፋት ሲያጠፋ ካየን ዝም ማለት እንደሌለብን፤ ጓደኞችንም ቢሆን ጥፋት ካጠፋ መምከር እንዳለብን ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር በሰዎች ላይ አድሮ ሲገስፀን የተባልነውን ሳንንቅ ተቀብለን ትእዛዝ መፈጸም ይገባናል።

አጥፍተን ሲቆጡን ደግሞ መናደድና ቂም መያዝ የለብንም። እንዲህ የምናደርግ ከሆነ ግን እግዚአብሔር ይቆጣናል ማለት ነው። ሌላው ትልቁ ነገር የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ማክበር እንዳለብን ነው። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዳትረሱ።

በሉ ልጆች! ለዛሬ በዚህ ይብቃን። በሚቀጥለው ጊዜ በክፍል ሁለት በሚኖረን ቆይታ ደግሞ ስለ ነቢዩ ኤርምያስ እንማራለን። ደኅና ሁኑ ልጆች!

# የተከለከለ እርድ

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

በአንዳንድ አጋጣሚዎች በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሊፈጸሙ የማይገባቸው አንዳንድ ተግባራት ሲፈጸሙ ስናይ ልንደነግጥ እንችላለን፡፡ ታዝበንም የምናልፋቸው በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሊተቹ ከሚገባቸው በማወቅ ወይም ባለማወቅ ከሚፈጸሙ ተግባራት አንዱ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ውስጥ የእንስሳት እርድ የመፈጸም ጉዳይ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ እንስሳት ደም ፈሶ ማየት በአጅጉ ሊያስተዛዝብ የሚችል ተግባር ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ ከደጀሰላሙ ጀምሮ እስከ ውስጠኛው ክፍል የተቀደሰ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ያልተባረከ፣ ለሥጋዊ ዓላማ የሚውል ምንም ዓይነት ቁስም ሆነ ተግባር ሊገኝ፣ ሊታይ አይገባም፡፡ በፍትሐ ነገሥቱ ‹‹በቤተ ክርስቲያን ላይ የተደፋፈረ ከእርሷ ዘንድ ካልሆነ በቀር ሊደረግ የማይገባውን የቤተክርስቲያን ሥራ የሠራ ሰው ቢኖር የተለየ የተወገዘ ይሁን›› … ‹‹በቤተ እግዚአብሔር ውስጥና በተቀደሱት ታቦቶች አጠገብ ግብዣ ለማድረግ መጥራት አይገባም ›› (አንቀጽ ፩፥፲ እና ፲፪) የተባለውን ልብ ይሏል፡፡

እንደሚታወቀው አምልኮተ እግዚአብሔር በሚፈጸምበት ቦታ መሥዋዕት ማቅረብ በሕገ ልቡናና በዘመነ ኦሪት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥርዓት ሆኖ ኖሯል፡፡ በሕገ ልቡና ዘመን ሰዎች ለእግዚአብሔር በሚሠሩት መሠዊያ ዙሪያ ይጸልያሉ፡፡ በዚያም የእንስሳት መሥዋዕትን አርደው የሚቃጠል መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ አቤል የበግ መሥዋዕት እንዳቀረበ ይታወቃል፡፡ ኖኅም ለእግዚአብሔር የእንስሳት መሥዋዕት አቅርቧል፡፡ ‹‹ኖኅም ለእግዚአብሔር መሠውያውን ሠራ፥ ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ ከንጹሓን ወፎችም ሁሉ ወሰደ፥ በመሠውያውም ላይ መሥዋዕትን አቀረበ፡፡ (ዘፍ ፰፥፳) አብርሃምም በታዘዘው መሠረት መሥዋዕትን አቅርቧል፡፡ ‹‹አብርሃምም ዓይኑን አነሣ፥ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው፡፡ (ዘፍ ፳፪ ፥ ፳፫)

እግዚአብሔር በኋላም በሙሴ በኩል ለእስራኤል የአምልኮ ሥርዓት እንዲሆን ያዘዘው የእንስሳት መሥዋዕት ነበር፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔርን በሚያመልኩበት በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት እንዲያቀርቡ እንደሚከተለው ታዘዋል፤ ‹‹እግዚአብሔርም ከመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ ሲል ተናገረው፦ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፦ ከእናንተ ማናቸውም ሰው ለእግዚአብሔር መባ ሲያቀርብ መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች ታቀርባላችሁ፡፡ መባውም የሚቃጠል መሥዋዕት ከላሞች መንጋ ቢሆን፥ ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀርባል፤ በእግዚአብሔር ፊት እንዲሠምር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበዋል፡፡ እጁንም በሚቃጠለው መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል፤ ያስተሰርይለትም ዘንድ የሠመረ ይሆንለታል፡፡ በሬውንም በእግዚአብሔር ፊት ያርደዋል፤ የአሮንም ልጆች ካህናቱ ደሙን ያቀርባሉ፤ ደሙንም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ባለው በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል፡፡ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት ይገፍፈዋል፥ በየብልቱም ይቈርጠዋል፡፡ የካህኑም የአሮን ልጆች በመሠዊያው ላይ እሳት ያነድዳሉ፥ በእሳቱም ላይ እንጨት ይደረድራሉ፤ የአሮንም ልጆች ካህናቱ የተቈረጡትን ብልቶች ራሱንም ስቡንም በመሠዊያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው በእንጨቱ ላይ ይረበርቡታል፤ የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን ግን በውኃ ያጥባል፤ ካህኑም ሁሉን የሚቃጠል መሥዋዕት የእሳት ቍርባን አድርጎ በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል፡፡ ቍርባኑም የሚቃጠል መሥዋዕት ከበጎች ወይም ከፍየሎች ቢሆን፥ ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀርበዋል፡፡›› (ሌዋ ፩፥፩–፲)

በዘመነ ብሉይ የእንስሳት መሥዋዕት ለጊዜያዊ የኃጢአት ሥርየት እና እግዚአብሔርን የማምለክ

መሥዋዕት ግን አልፏል፡፡ ‹‹እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፡፡ ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤›› (፩ኛ ቆሮ ፭፥፯) ተብሏል፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤት ነች፡፡ ስለዚህ በቤቱ የሚሰጠው የእርሱ ሥጋና ደም ነው፡፡ ‹‹የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም፡፡›› (ዕብ. ፱፥፲፪) እንደተባለ፡፡

**አንዳንዶች ታቦታት ከቤተ መቅደስ ወጥተው በታቦት ማደሪያ በሚያድሩበት ጊዜ ምእመናን በማግስቱ አጅበው ለማስገባት ‹‹እልል...›› እያሉ ሲከተሉ ካህናቱ የበጉን ደም ረግጠው እንዲያልፉ በደጃፉ በግ አርደው ደሙን አፍሰው እንደ መሥዋዕት እንዲቆጠርላቸው የሚደክሙ ሰዎች ያጋጥማሉ፡፡ ይህ የኦሪት ሥርዓት እንጂ የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ስላልሆነ በተቻለ መጠን እንዲታረም ሁሉም ወገን በአጋጣሚው ሁሉ ሊያስተምር ይገባል፡፡**

በዚህም ምክንያት የጌታ ሥጋና ደም መሥዋዕት ሆኖ በሚቀርብባት ቅድስት ቤተክርስቲያን ቅጽር ውስጥ በየትኛውም ምክንያት የእንስሳት እርድ ፈጽሞ መገኘት የሚያስተች ከሥርዓት የወጣ ተግባር ነው፡፡ አንዳንዶች በዓላት ሲሆኑ ታቦት ወጥቶ በሚገባበት ዕለት በቤተክርስቲያን ደጃፍ በግ አርዶ ደም ማፍሰስን እንደ ሥርዓት ይዘውት ለተውልድ ሲያስተላልፉት ይታያል፡፡ በተለይ በአንዳንድ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ይህ ነገር ሊያጋጥም የሚችል ነው፡፡ ለአንዳንዶች ታቦታት ከቤተ መቅደስ ወጥተው በታቦት ማደሪያ በሚያድሩበት ጊዜ ምእመናን በማግስቱ አጅበው ለማስገባት ‹‹እልል...›› እያሉ ሲከተሉ ካህናቱ የበጉን ደም ረግጠው እንዲያልፉ በደጃፉ በግ አርደው ደሙን አፍሰው እንደ መሥዋዕት እንዲቆጠርላቸው የሚደክሙ ሰዎች ያጋጥማሉ፡፡ ይህ የኦሪት ሥርዓት እንጂ የሐዲስ ኪዳን ሥርዓት ስላልሆነ በተቻለ መጠን እንዲታረም ሁሉም ወገን በአጋጣሚው ሁሉ ሊያስተምር ይገባል፡፡

ሌላው ምእመናን የበግ ወይም የበሬ እርድ የሚፈጽሙት በበዓላት ድግስ ደግሶ ለማብላት በማሰብ ሲሆን ይህ የሚበረታታ ሆኖ ሳለ እርዱን ግን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን መፈጸም ለትዝብት የሚዳርግ ይሆናል፡፡ አንዳንዴም ሀገር አቋርጠን ወንዝ ተሻግረን መንፈሳዊ ጉዞዎችን ለማድረግ ሔደን እንዲህ ያሉ ከሥርዓት ያፈነገጡ ነገሮችን በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ያለመስጠት ልምዶች ይታያሉ፡፡ እነዚህ ሆነ ተብለው ባይደረጉም የሥርዓት ጥፋት ስለሚያስከትል ቶሎ ማረም የሚገባ ነው፡፡

ሌላው አሳዛኙ ነገር ካህናት ተሰባስበው በቅርጫ ስም የገዙትን እንስሳት በቅጽረ ቤተክርስቲያን ሲያርዱ መታየታቸው ነው፡፡ በአዲስ አበባ አንዳንድ አጥቢያዎችም ጭምር ይህ ሲሆን መመልከታችን አስተዛዛቢ ነው፡፡ ካህናት በቤተ ክርስቲያን ለሚከበሩ በዓላትም ሆነ ለቤተሰባቸው የሚያዘጋጁትን እርድ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን እንዳይፈጸም ግንባር ቀደም ሥርዓት አስከባሪ ሆነው መታየት አለባቸው፡፡ ለበዓሉ የሚያዘጋጁትን እርድ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውጪ በማድረግ ተረፈ እርዱንም በመቅበር፣ በማቃጠል አሊያም አርቆ በመጣል የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና እና ቅድስና ሊጠብቁ ይገባል፡፡

# ትዳሬ ሊፈርስ ነው ምን የሻለኛል?

**ክፍል ሁለት**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***

ትዳር የሚታዘቡት ሳይሆን የሚሠሩለት ሕይወት ነው። ለጋብቻ /ትዳር/ የምንሠራለት በእጮኝነታችን፣ በሠርጋችን በጫጉላችን ጊዜ ብቻ አይደለም። የዕድሜ ልክ ሕይወት እንደሆነ አምነን ቃል የገባንለት በመሆኑ ዕድሜ ልክ በትዕግሥት የምንሠራለት ሕይወት ነው። መጽሐፍ ‹‹ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት›› /ቆላ ፫፥፳፫/ እንዳለ በቁም ነገር ለያዝነው ሕይወት ከልብ ልንተጋለት ይገባል።

ፍቅርንና ሰላምን ጠብቀን ለመቆየት ከመሰላቸትና ከመናናቅም ለመዳን ጋብቻችንን በፍቅር አድሶ ሳቢ ማድረግ ይጠይቃል። ይሄን አለማድረግ ግን ስንፍና ነው። ጋብቻን በስንፍና መያዝም ችግሮችን ያስከትላል። በስንፍና ምክንያት በጋብቻ ላይ የሚመጣውን ጣጣ ደግሞ ሰነፎች ሊሸከሙት አይችሉም። በተለይ በጋብቻ እናገኘዋለን ብለው ከጠበቁት በታች የሆነ የኑሮ ጣዕም ካጋጠማቸው የበለጠ ይታወካሉ። የተሻለ የኑሮ ጣዕም በሁለቱም ተጋቢዎች ትጋት የሚመጣ መሆኑን ዘንግተው አንዱ ከሌላው የሚጠብቅ ሲሆን ደግሞ በዚህ መሰናክል አያልፉም።

ለመጣው ፈተና መፍትሔው ፍቺ ነው ብሎ ማሰብም ለበለጠ ፈተና ያጋልጣል። ጠያቂያችንም እንደ መፍትሔ የወሰዱት ፍቺ እንደሚያስቡት የተፈቀደ፣ የተመረጠ፣ የሚጠቅምና የሚስማማም ሕይወት አይደለም። ፍቺ መፈጸምዎን ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚስማማ ልቡና ለማግኘት ያበቃል ብለው መገመትዎም ትክክል አይደለም። በፍቺ የተሰበረ ትዳር አስቀምጦ፤ በፍቺ ያዘነ ቤተሰብ በትኖ በእግዚአብሔር ፊት በመልካም መንፈስ መቆም አያስችልም። ስለዚህ ከብዙ ነገሮች አንጻር ፍቺ ለእርስዎ የተገባ አለመሆኑን እንዲረዱ ጠቃሚ ነጥቦችን እናሳስብዎ።

የመጀመሪያው ነገር ለክርስቲያናዊ ሕይወትዎ የሚሳሱለት ስለሆነ ለዚህ የተለያዩ ማሳያዎችን ልንጠቅስልዎ እንችላለን። የክርስቲያናዊ ሕይወት ተጋድሏችን የሚጀምረው በቤታችን ያለውን ቅራኔ በማራቅ መልካም ሰላም በማስፈን ነው። ለዚህም ትልቁ መፍትሔ ጸሎትን ማድረግ፣ ያደርጉ ከነበረም አብዝተው መትጋት፣ በገዳማትና አድባራት በሚጸልዩ አባቶች ለእርስዎና ለቤተሰብዎ ጸሎት ማስያዝ እና በመንፈሳዊ ሕይወት ሲጸኑ ይገባል። በቃለ እግዚአብሔርም ራስዎንና ቤተሰብዎን ለማነጽ ከምንጊዜውም በላይ መትጋት፤ ትናንትም ሲያደርጓቸው ከነበሩ መንፈሳዊ የሕይወት እርምጃዎች ዘግይተውና ቀዝቅዘው ከሆነ ለሕይወትዎ ሙቀት ለመስጠት መጀመር አለብዎ።

እንዲሁም ባለቤትዎና ራስዎ በተለያዩ አጋጣሚዎች በጋራ ለቃለ እግዚአብሔር የቀረባችሁ እንድትሆኑ ዕድሎችን ሁሉ መጠቀም። በነፍስ አባትዎም፣ በተለያዩ የጉባኤ አጋጣሚዎች ወደ መልካም መንፈስ የሚመልስ የቃሉን በረከት ለመሳተፍ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር መሞከር ይገባል። ሌላው ባለቤትዎ ያጎደሉትን ነገር እንዲያሟሉ በእርስዎ በኩል ያጎደሉት ነገር ግን ያላስተዋሉት ነገር ካለ በተቻለ መጠን ለዘብ ብለው በሚደረጉ የቤተሰብ ምክክሮችን፣ መፍትሔ መወያየት፣ በተለይ ከንስሓ አባት ጋር መመካከር እንዲሁም በጾም እና በጸሎት በመትጋት፣ እግዚአብሔርን አጥብቆ መማጸን ያስፈልጋል።

እርስዎ ቀላል አድርገው ያሰቡት ፍቺ ግን ሕግ የሚተላለፍ አማራጭ ሲሆን፣ በቅድሚያ ከእግዚአብሔር የሚለይዎትና የመንፈሳዊ ሕይወት ቀውስ የሚያስከትል ይሆናል። ጌታችን በጽኑ ቃሉ ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።›› /ማቴ ፭፥፴፪/ ብሎ በሕገ ወንጌል የጸና ትእዛዝ ስለሰጠ ከዚህ መተላለፍ ጌታችንን ማሳዘን ነውና። ስለዚህ የመጀመሪያው መንፈሳዊ ጉዳት ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

ሌላው ወሳኝ ነገር እንደሚወዷቸው የተናገሩላቸው ልጆችዎ በእናትና አባት መፋታት ፍጹም ይጎዳሉ እንጂ አይጠቀሙም። ልጆችዎን ፈልገው እናታቸውን መግፋት፣ ልጆችዎን የሚጎዳ እንጂ የሚጠቅም አይሆንም። ልጆችዎን የሚወዷቸው ከሆነ ትዳርዎን በትዕግሥት ይዞ መቆየትን መምረጥ ትልቅ አስተዋይነት ነው። ልጆችዎ ነፍስ ስላወቁ በፍቺው የማይጎዱ አድርገው ማሰብዎም ትክክል አይሆንም። ልጆች ባደጉ ቁጥር የበለጠ ለምን፣ እንዴት ብሎ በማሰብ እንደሚጠመዱና ለጭንቀት ተጋላጭ እንደሚሆኑ ማሰብ ይገባል።

ልጆች ፍቺ ምን ማለት እንደሆነ ካለማወቅ ጀምሮ ምክንያቱ ምን እንደሆነ እስከማሰላሰል በመድረስ በሚፈጠርባቸው የአሳብ እንግልት በቅድሚያ የአእምሮ ጉዳት ይደርስባቸዋል፤ ከአንዱ ወላጃቸው ተነጥለው ለማደግም ያስገድዳቸዋል፤ የሚያድጉበት ሁኔታም የተሟላ ቤተሰባዊ ስሜትም አያሳድርባቸውም፤ የአንድ ወገን ናፍቆትም ሊያንገላታቸው ይችላል፤ የበታችነት ስሜትም

ሊያድርባቸው ይችላል፤ የአእምሮም ዕረፍት ያጣሉ:: ስለዚህ ጠያቂያችን ይህንና ከዚህ ጋር ተያይዞ በልጆች ላይ ሊከሠት የሚችለውን ዘርፈ ብዙ የአእምሮ ስሜት፣ የማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት ቀውስ ሁሉ ካጤኑ ለመታገሥ አቅም ያገኛሉ::

ጠያቂያችን ሌላው ሊታለሉበትና ሊሞኙበት የማይገባው ጉዳይ ‹‹ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል::›› /መክ ፬÷፱/ ብሎ ጠቢቡ እንደተናገረ ትንሽም ይሁን ትልቅ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ በጋራ ሆናችሁ የገነባችሁት ሕይወት መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ቁሳዊ ሀብት ንብረትም ያስገኛል:: ጋብቻ ሲፈርስ ሰዎች የሚጎዱት በነፍስ ብቻ አይደለም፤ ሥጋዊ ኑሮአቸውም ስኬታማ አይሆንም:: በነገር ሁሉ ብርቱ የሚሆኑበትንም አቅም ያጣሉ:: አርሰው ቢያድሩ፤ ነግደው ቢኖሩ፤ ተምረው ተመራምረው ሀገርን ሊያቀኑ ቢቆርጡ፤ ከአንድ ይልቅ ሁለት መሆኑ የበለጠ ያበረታል:: ይህን ያጣጣሙትን ወይም ለማጣጣም ጥበብ ያጡበትን አቅም በፍቺ ውስጥ እንዳያጡት በማስተዋል ማሰብ እጅግ በጣም ጥሩ ነው::

‹‹መፋታት ይፈቀዳል›› በሚል ሰበብ በሚረባውም በማይረባውም ጉዳይ ጋብቻን ማፍረስ ተገቢ አይደለም፤ በመሆኑም የትዳር መሠረትን እንዲሁም አንድነታችንን ማጥበቅ ይገባናል:: እንደዚህ ብናደርግ በምድርም በሰማይም እንጠቀማለን:: ፍቺን በተመለከተ የጋብቻ ሕይወት ሃይማኖትን፣ ንጽሕናን እንደዚሁም መንፈሳዊ ሕይወትን የሚፈታተን እንደ ዝሙትና ሃይማኖትን መለወጥ ዓይነት ኀጢአት ወይም ሞት ካልመጣ በቀር በአንድነት እንደ ጸና ይኖራል እንጂ በቀላሉ አይፈርስም:: ስለዚህም በጋብቻ አንድነት ውስጥ መለያየት (ፍቺ) እንዳይኖር በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተደንግጓል::

ውድ ጠያቂያችን መፋታት የሚለው ሐሳብ ሲነሣ መፋታት የሚቻለው ምን ሲሆን ነው ብሎ ነገሩን በጥልቀት ማሰብም ተገቢ ነው:: እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ፍቺ የሚፈቀድባቸውን ምክንያቶች በውል መገንዘብ ይገባል:: ፍቺ ከሚፈቀድባቸው ምክንያቶች አንዱ ዝሙት ነው:: ዝሙት በጋብቻ ውስጥ ያሉትንም ሆነ በጋብቻ ውስጥ የሌሉትን በአጠቃላይ የሚፈትን ሲሆን (በዘፀ. ዘፀ. ፳÷፲፬) ‹‹አታመንዝር›› ተብሎ እንደታዘዘው ዝሙት መሥራት ኃጢአት ነው:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (በማቴ. ፭÷፴፪) “ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል” እንዳለ ባልና ሚስት በፍቺ ሊለያዩ የሚችሉት በዝሙት ምክንያት ሲሆን ይህም ከትዳር አጋሩ አልፎ (አልፋ) ወደ ሌላ የሚሄድ (የምትሄድ) ካለ (ካለች) ስለ ጋብቻ ክቡርነት፣ ስለ ሥጋ ወደሙ ቅድስና ሲባል መፋታት ይፈቀዳል::

ሁለተኛው ምክንያት ከሁለቱ ጥንዶች መካከል አንደኛው ወገን በሞት ሲለይ በሕይወት የቀረው ወገን ለብቻው መኖር የማይችል ከሆነ ለሁለተኛ ጊዜ ማግባት ይፈቀዳል:: ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ‹‹ . . . ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና ፤ ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባልዋ ከሆነው ሕግ ተፈትታለች›› (ሮሜ. ፯÷፪) እንዳለው በሕይወት ያለው ወገን ለብቻው ራሱን ጠብቆ መኖር ካልቻለ ማግባት ይችላል::

ሦስተኛው በሁለት የትዳር አጋሮች መካከል ፍቼ የሚፈቀድበት ምክንያት በመካከላቸው የሃይማኖት ልዩነት ሲኖር ነው:: ሃይማኖት ለሁለት ባልና ሚስት የጋራ ጉዳይ መሆን አለበት:: መጽሐፍ ‹‹ሁለቱ አንድ ሥጋ ናቸውና ወደፊት ሁለት ሊባሉ አይችሉም›› እንዲል በጋብቻ የተጣመሩ ባልና ሚስት ሃይማኖታቸው የተለያየ ከሆነ በሃይማኖት ልዩነት ምክንያት ፍቺ ይፈቀዳል:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ‹‹ከማያምኑ ጋር በማያመች አካሄድ አትጠመዱ›› ፪ኛ ቆሮ. ፮÷፲፬ እንዳለ በእምነት ከማይመስለን ሰው ጋር በአንድ ጣሪያ ሥር መኖር ራስንና የቤተ ክርስቲያንን ክብር ማቃለል ነውና በጋብቻ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ጥምረት አይፈቀድም:: በመሆኑም ፍቺ ከሚፈቀድባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የሃይማኖት ልዩነት ነው ማለት ነው::

ውድ ጠያቂያችን ከላይ በዝርዝር ለማንሣት እንደሞከርነው ከተነሡት ምክንያቶች ውጪ በራስዎ ፈቃድ እንደ መፍትሔ ያሰቡትን ፍቺን በእግዚአብሔር ረድኤት ከሐሳብዎ ሊያርቁት፤ ፈጽሞም ሊሽሹት ይገባል:: ጋብቻ የዕድሜ ልክ ስጦታና ከሁለት አንድ ሆነው የሚቆዩበት ልዩ ምሥጢር ነውና:: አብሮ በመኖር ውስጥ ይቅርታን በመስጠትና በመቀበል፣ በመቻቻል፣ ሕይወትን ጣፋጭ ማድረግ ይኖርብዎታል:: ከዚህ በተጨማሪም በጋብቻ ጉዳይ ላይ ከሚያማክሩ የሥነ ልቡና ባለሞያዎች የምክር አገልግሎት ማግኘት እንዲሁም ከንስሓ አባትዎ ጋር ቶሎ ቶሎ በመገናኘት በጉዳዩ ላይ በደንብ መወያየት ንስሓ መቀበል መጾም እና መጸለይ ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግዳሮት ይታደግዎታል:: በመጨረሻም እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት ‹‹መፋታትን እጠላለሁ›› (ሚል. ፪÷፲፮) ያለውን ቃሉን በእዝነ ልቡናዎ ሊይዙ ይገባል:: በመጨረሻም ውድ ጠያቂያችን የወደፊት የትዳር ሕይወትዎ የተቃና ይሆን ዘንድ አምላከ ቅዱሳን በረድኤት ይኅብኝዎ እንላለን::